
# የሴቶች ግንባር ቀደም ተሳትፎ በትራኮማ ቁጥጥር

በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የተዘጋጀ

## የአሠልጣኞች መመሪያ



# The Leading Role of Women in Trachoma Control

## Trainer's Guide

Prepared by the Carter Center-Ethiopia

ነሐሴ 1996
August 2004

# የሴቶች ግንባር ቀደም ተሳትፎ
# በትራኮማ ቁጥጥር

በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የተዘጋጀ

## የአሠልጣኞች መመሪያ

# The Leading Role of Women in Trachoma Control

## Trainer's Guide

**Prepared by The Carter Center-Ethiopia**

## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ ........................................................................................ | |
| ክፍል 1:- የማሠልጠኛ መመሪያው ዝግጅት ዓላማ ....................................... | 1 |
| 1.1 የማሠልጠኛ መመሪያው አጠቃቀም ........................................ | 2 |
| 1.2 የማሠልጠኛ ዘዴዎችና ስልቶች ................................................ | 3 |
| ክፍል 2:- የትራኮማ በሽታ መሰረታዊ እውነታዎች ...................................... | 4 |
| 2.1 ትራኮማ ምንድን ነው? ..................... ...... ................................ | 4 |
| 2.2 የትራኮማ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች ........................................... | 4 |
| 2.3 የትራኮማ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች ........................................ | 5 |
| 2.4 የትራኮማ በሽታን ስርጭት የሚያባብሱ ሁኔታዎች ............................................................ | 6 |
| 2.5 የትራኮማ በሽታ የጥቃት ደረጃዎች ............................................ | 9 |
| 2.6 የትራኮማ በሽታን ለመከላከልና ብሎም ለማጥፋት የሚያስችሉ የተቀናጁ ስልቶች ............................... | 10 |
| ክፍል 3:- ትራኮማ ትኩረት የሚሻ የሴቶች ጤና ችግር ...... ........................ | 17 |
| 3.1 የሴቶች ጤና አጠቃላይ ሁኔታ ....................................................... | 17 |
| 3.2 የትራኮማ በሽታ የሴቶች አንገብጋቢ ችግር ነው ............................................................ | 18 |
| 3.3 በተዛባ የስራ ክፍፍል ምክንያት የሴቶች ለትራኮማ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚ ....................................................... | 20 |
| 3.4 የትራኮማ በሽታ በሴቶች ላይ የሚያስከትለው ጫና .................... | 24 |
| 3.5 የሴቶች ዓይነ ስውርነት የሚያስከትለው ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ .................................................. | 25 |
| 3.6 የሴቶች ዓይነ ስውርነት በቤተሰብ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ........................................................... | 25 |
| 3.7 በትራኮማ ሕክምና ላይ የሚደረግ የባህልና የጾታ ተጽዕኖ .......... | 26 |

**ክፍል 4፡- ትምህርቱ የሚያካትታቸው ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች** ...................... 28

4.1 ስለ ንጹህና በቂ የውሃ አቅርቦት ...................................................... 28

4.2 የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ....................................... 29

4.3 የበራሪ ነፍሳትና ቆርጣሚ እንስሳት ቁጥጥር ................................. 31

4.4 የመጸዳጃ ቤት አስፈላጊነት፣ አሠራርና አያያዝ ............................. 34

4.5 ለጤና ተስማሚ የሆነ ቤት አሠራርና አጠባበቅ ............................ 35

4.6 የመኖሪያ ቤት ንጽህና አጠባበቅ ...................................................... 36

**ማጠቃለያ** ........................................................................................... 38

**ዋቢ መረጃዎች** .................................................................................... 39

# ምሥጋና

***ካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ*** ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የትራኮማ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ሕብረተሰቡ ለዓይነ ስውርነት እንዳይጋለጥ ያዘጋጀውን መርሃ ግብር ተግባራዊ ለማድረግና በተለይም ይህንን የአሰልጣኞች መመሪያ ለማዘጋጀትና ለማሳተም የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ በመሸፈን ላደረገው ትብብርና የገንዘብ ድጋፍ *ለላይንስ ክለብ* ኢንተርናሽናል ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል።

በተጨማሪም ይህ ሰነድ ተስማሚ የአሰልጣኞች መመሪያ እንዲሆን መረጃዎችን በማቀናበርና በአማርኛ በማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረትና አስተዋጽኦ ያደረጉትን የሙያ አማካሪዎች ዶ/ር አዳነች ኪዳነ ማሪያምንና አቶ ጠና አበረን ያመሰግናል።

*ካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ*

## መግቢያ

ጤንነት የተሟላ የአካል፣ የአዕምሮና የማኅበራዊ ኑሮ ደህንነት ነው። በሀገራችን ከሚገኙት የጤና ችግሮች መካከል ከ75% በላይ የሚሆኑት ተላላፊ በሽታዎች ናቸው። እነዚህ የጤና ጠንቆች በኅብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የጤና መታወክ፣ የማኅበራዊ ቀውስ፣ የስነልቦና ችግር፣ የአካል ጉድለትና የሞት አደጋ በማድረስ ላይ ይገኛሉ። በአጠቃላይ ድህነትና ኋላ ቀርነት፣ የምግብ እጥረትና የንጽህና ጉድለት፣ ማንኛውንም በሽታ እንደሚያባብስ ይታወቃል።

በግልና በአካባቢ ንጽህና ጉድለት ምክንያት ከሚተላለፉት በሽታዎች መካከል የትራኮማ በሽታ በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጥቃት እያደረሰ ነው። ከጥናት ዘገባዎች በተገኘው መረጃ መሠረት በዓለም ላይ በትራኮማ በሽታ ምክንያት 6 ሚሊዮን ሰዎች በዓይነ ስውርነት የተጠቁ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የመጋለጥ አጋጣሚ እንዳላቸው ይገመታል። 146 ሚሊዮን ተጨማሪ ሰዎች በብርቱ የትራኮማ በሽታ (Active Trachoma) የተያዙ ስለሆነ በአስቸኳይ የሕክምና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ከነዚህም መካከል 75% የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።

የትራኮማ በሽታን በተመለከተ በአፍሪካና በሃገራችንም ጭምር አንዳንድ መሠረታዊ የአሰሳ ጥናቶች ተካሂደዋል። ከተለያዩ ጥናቶች በተገኘው ውጤት መሠረት ሴቶች የትራኮማ ችግር ላለባቸው ልጆች በየቀኑ በማጥባት፣ በማቀፍ፣ በማጠብና ሌሎችንም አስፈላጊ እንክብካቤዎች በመስጠት ከወንዶች በበለጠ ለትራኮማ በሽታ የተጋለጡ ናቸው። በመሆኑም በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች በትራኮማ ምክንያት አይነ ስውር ከሚሆኑ ሰዎች መካከል 75% ሴቶች እንደሆኑም ታውቋል።

በሀገራችን ስለ ትራኮማ በሽታ የስርጭት መጠን በብሔራዊ ደረጃ የተደረገ ጥናት የለም። ይሁንና አልፎ አልፎ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ጥቂቶቹን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የተካሄደ አንድ ጥናት እንደሚጠቁመው የብርቱ ትራኮማ በሽታ (Active Trachoma) ስርጭት ዕድሜያቸው 1-10 ዓመት በሆኑ ልጆች ላይ ከ51%-79% እንደሚደርስ ታውቋል። በሌላ በኩል ደግሞ ስር የሰደደ የትራኮማ በሽታ (Chronic Trachoma) የስርጭት መጠን ከ 3 - 3.2 እንደሆነ የጥናቱ ዘገባ ያብራራል።

በደቡባዊ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተደረገ ሌላ ጥናት የትራኮማ በሽታ የሥርጭት መጠን በመላው ህብረተሰብ ውስጥ 24.5% መድረሱ የታወቀ ሲሆን እድሜያቸው ከ1 - 10

ዓመት በሆኑ ልጆች ላይ 35.7% መሆኑ ታውቋል:: ስር በሰደደ የትራኮማ በሽታ ምክንያት የዓይን ቆብ መቆራፈድና ወደ ውስጥ የመቀልበስ ችግር (Entropion) የሚያስከትለው የጤና ችግር ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ጎልቶ ይታያል:: በዚህ በሽታ የሚጠቁት 2/3ኛ የሚሆኑት ሴቶች የትራኮማ በሽታ ተጠቂ ከሆኑ ልጆች ጋር የቅርብ ግንኙነት ስላላቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል::

በ1993 ዓ.ም ኦርቢስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ የተባለ ድርጅት ባቀረበው ጥናታዊ ዘገባ መሠረት ተንቀሳቃሽ የዓይን ቆብ ቀዶ ህክምና አገልግሎት በተሰጠባቸው ስፍራዎች ስር በሰደደ የትራኮማ በሽታ የሚሠቃዩና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑት ሴቶች ከ75% በላይ መሆናቸው ተዘግቧል::

የካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የትራኮማ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ህብረተሰቡን ከአይነ ስውርነት ለማዳን መርሀ ግብር ነድፎ በሚንቀሳቀስበት በአማራ ብሔራዊ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን በዕብናት፣ በእስቴ፣ በደራና በስማዳ ወረዳዎች የትራኮማ በሽታን የስርጭት መጠን ለማወቅና የተቀናጀ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ በባለሙያዎች የተደገፈ የአሰሳ ጥናት ተካሂዶ ነበር::

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ከላይ በተጠቀሱት ወረዳዎች እድሜያቸው ከ1-10 ዓመት የሆነ በብርቱ የትራኮማ በሽታ የተጠቁ ልጆች ከ81.2 - 96.7% የደረሰ ሲሆን፣ እድሜያቸው ከ39 ዓመት በላይ በሆኑ ሴቶች ላይ ስር በሰደደ የትራኮማ በሽታ ወይም የዓይን ቆብ ቁስለትና መቆርፈድ እንዲሁም ወደ ውስጥ የመቀልበስ ችግር (Entropion) ያለባቸው ሴቶች ከ18.3 - 23.2% የደረሰ መሆኑ ታውቋል:: ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ ክልል በሚገኙ በአራት ዞኖችና በ15 ወረዳዎች እድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች በሆኑ ልጆች ላይ በተደረገው ጥናት በተገኘው ውጤት መሠረት የትራኮማ በሽታ የስርጭት መጠን ከ36-89% የደረሰ መሆኑ ታውቋል::

ከላይ እንደተገለጸው በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተደረጉት የናሙና ጥናቶች በተገኘው ውጤት መሠረት የትራኮማ በሽታ በአጠቃላይ በህብረተሰቡ በተለይም በሴቶችና በሕፃናት ላይ አሳሳቢ የጤና ችግር መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል:: በመሆኑም በግልና በአካባቢ ንጽህና ጉድለት ምክንያት የሚከሰተው የትራኮማ በሽታ ከሚያስከትለው የህመም ስቃይ ባሻገር በተለይ በሴቶች ላይ እያደረሰ ያለው የዓይነ ስውርነት ችግር የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች ለልመናና ለጎዳና ተዳዳሪነት እየዳረጋቸው ነው::

የዚህ የማሰልጠኛ መመሪያ ዝግጅት ዋና ዓላማ ስለ ትራኮማ በሽታ መሠረታዊ እውነታዎችና በተለይም በሴቶች ላይ ስለሚያስከትለው የጤና፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ተጽእኖ ለሕብረተሰቡ መሠረታዊ ግንዛቤ ለማስጨበጥና እራሱን እንዲጠብቅ ለማድረግ ነው:: መመሪያው አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ለግንዛቤ ያመች ዘንድ ስእላዊ መግለጫዎች እና መልመጃዎች ታክለውበታል::

ስለዚህ የትራኮማ በሽታ የሚያስከትለውን የጤና፣ የማኀበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የአካል ጉድለት ጠንቅ በመንደር አቀፍ ደረጃ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ በዕቅድ አወጣጥና በአመራር የችግሩ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የሆኑ ሴቶች ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ይህን መርሃ ግብር እውን ለማድረግ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ በልዩ ልዩ ሲቪል ማኀበራት ተደራጅተው የሚገኙ ወገኖችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የሃገር ሽማግሌዎችን፣ አባወራዎችና እማወራዎችን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ መምህራንና ተማሪዎችን፣ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ ወጣቶችን ከሁሉም በላይ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ማሳተፍ አስፈላጊና ተገቢም ነው::

ክፍል አንድ :-

## የማሠልጠኛ መመሪያው ዝግጅት ዓላማ

የማሰልጠኛ መመሪያው ዝግጅት ዋና ዓላማ የትራኮማ በሽታ በህብረተሰቡ በተለይም በሴቶች ላይ እያስከተለ ያለውን የጤና መታወክና የአይነ ስውርነት ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ስልጠና ለመስጠት ነው::

### የማሰልጠኛው መመሪያው ዝርዝር ዓላማዎች

- የትራኮማ በሽታ ዋናው መንስዔ በአጠቃላይ የግልና የአካባቢ ንጽህናና በተለይም የፊት ንጽህና አጠባበቅ ጉድለት በመሆኑ በሽታው በስፋት በተሰራጨባቸው አካባቢዎች ለመላው ህብረተሰብ በተለይም ግንባር ቀደም ተጠቂ ለሆኑት ሴቶች የባሕሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል መሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ለመስጠት፣
- የትራኮማ በሽታ ዋና አስተላላፊ ዝንቦች በመኖሪያ አካባቢ እንደ ልብ እንዳይራቡ የግልና የአካባቢ ንጽህናን በአግባቡ ለመጠበቅ ፣
- በተለይም የፊትና የግል ንጽህናን ለመጠበቅ የውሃ መገኛ ምንጭ በመኖሪያ አቅራቢያ መኖር ወሳኝ በመሆኑ ህብረተሰቡ ተባብሮ ከቅርብ ርቀት በቂ የውሃ ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ለማመቻቸት፣
- የውሃ እጥረት በአካባቢው ቢኖርም እንኳን በየቀኑ የፊት ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስፈልገው የውሃ መጠን አነስተኛ ስለሆነ የችግሩን አንገብጋቢነት ተገንዝቦ ቅድሚያ መስጠት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ለመላው ቤተሰብና በተለይም ለሴቶች በቅድሚያ ለመስጠት፣
- ደረቅም ሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ባልተመቻቸበት ወይም በአግባቡ ባልተለመደበት በገጠሩ ሁኔታ ሰዎች ማንኛውንም የቤት ጥራጊ የከብት እበት፣ የሰው ሽንትና አይነምድር በአግባቡ የሚወገድበትን ሁኔታ ለማሳወቅ መሠረታዊ የጤና ትምህርት ለመስጠት፣
- በየገጠሩ በዘልማድ በየአካባቢው እዳሪ የመውጣትን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማስወገድና በተለይም ሕፃናትን ካጸዳዱ በኋላ አይነምድሩ ለዝንብ እንዳይጋለጥ የሚቀበርበትን ወይም በአግባቡ የሚወገድበትን ዘዴ ለማስተማር፣
- በቤት አሰራር ጉድለት ምክንያት ሴቶች ምግብ በሚያበስሉበት ጊዜ ዘወትር ለከፍተኛ የጪስ አደጋ ስለሚጋለጡ እና የዓይን ጤና ችግር ስለሚያጠቃቸው ቢቻል የተለየ የጪስ ቤት ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን፣ አሊያም በቂ መስኮት ያለው ቤት

መስራት ችግሩን ሊያቃልለው እንደሚችል ለአባወራዎችና ለመላው ቤተሰብ ለማስገንዘብ፣

- የትራኮማ በሽታ አንዱ መንስዔ በአንድ ቤት ውስጥ ተፋፍጎ የመኖር ችግር ስለሆነ ይህንን ችግር ለማቃለል በተቻለ መጠን ለመኖሪያ፣ ለምግብ ማብሰያ፣ ለእንስሳት ማደሪያ የተለያዩ ክፍሎች እንዲኖሩ ማድረግ ችግሩን ሊቀንሰው እንደሚችል ለማስረዳት፣
- በአጠቃላይ ሴቶች የሕፃናት አሳዳጊና ተንከባካቢ፣ የቤት ሰራተኛ፣ ለውሃም ሆነ ለማገዶ አቅርቦት ብቸኛ ተጠያቂ ያደረጋቸውን የተዛባ የሥራ ድርሻ በሂደት በመለወጥ ወንዶች ይህንን የጋራ ችግር ለማቃለል የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስገንዘብ፣
- በአዲሱ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ተመድበው የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች ይህንን መመሪያ እንዲጠቀሙት ለማድረግና የመሳሰሉት ናቸው::

## 1.1 የማሠልጠኛ መመሪያው አጠቃቀም

የትራኮማ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልጠና ለመስጠት ይህ መመሪያ መሠረታዊ ትምህርት ለሌላቸው ወይም አነስተኛ ግንዛቤ ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ሴቶች እንዲውል ታስቦ ነው:: ትምህርቱን የሚሰጡት የሕብረተሰብ የጤና ባለሙያዎች ከሁሉ አስቀድሞ የሚከተሉትን ፍሬ ሃሳቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል::

1. የትምህርቱ የአቀራረብ ስልት የተሳታፊዎችን ግንዛቤ፣ ደረጃና ስብጥር ግምት ውስጥ ያስገባ፣
2. የአካባቢው ሕብረተሰብ ሊረዳው ከሚችለው ቋንቋ ጋር የተጣጣመ ወይም የአካባቢ ምሳሌዎችን ያካተተ፣
3. የትራኮማ በሽታ በአካባቢው ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ የሚያመላክት ተጨባጭ መረጃ የያዘ፣
4. ትምህርቱ በሚሰጥበት ጊዜ የትራኮማ በሽታ በአካባቢው ያደረሰውን ጥቃት በተጨባጭ ማስረጃ ማንጸባረቅ የሚችል ወይም ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ያካተተ፣
5. የስልጠናው አቀራረብ አጋዥ ሰነዶችን (ስዕላዊ መግለጫ፣ የፊልም ትርኢትና የሰርቶ ማሳያ ቁሳቁሶችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል)::

## 1.2 የማሰልጠኛ ዘዴዎችና ስልቶች

በአጠቃላይ ስለጤና አጠባበቅ እና በተለይም ስለ ትራኮማ በሽታ ለህብረተሰቡ ለማስልጠን የተዘጋጀ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከህብረተሰቡ ፊት ከመቅረቡ በፊት ስለሚያስተምረው ትምህርት በአግባቡ መዘጋጀት ይኖርበታል:: ለትምህርት ዝግጅቱ የሚረዱ ዋና ዋና ጉዳዮች ወይም ነጥቦች ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል::

ሀ. **የትምህርቱን ዓላማ ማወቅ:-** የትምህርቱ ዓላማ ሲነደፍ የሚከተሉትን አበይት ነጥቦችን ማካተት ይኖርበታል::

1. በተወሰነ ርዕስ ላይ ያተኮረ (Specific) ለምሳሌ ስለዝንብ፣ ስለፊት መታጠብ፣ ዝንቦች ስለሚያርፉበት ስፍራ ወዘተ
2. የትምህርት ዓላማው ስኬት በቁጥር ወይም በዓይነት የሚለካ (Measurable) ለምሳሌ ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ የሚያስገኘው የባህሪ ለውጥ
3. ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ (Realstic) ለምሳሌ የትራኮማ በሽታ በአካባቢው ህበረተሰብ ላይ ያስከተለውን ጥቃት በምሳሌ ማስረዳት መቻል፣
4. በጊዜ የተወሰነ (Time Bound) ለምሳሌ ከተወሰነው ርዕስ ውጪ ያለ አግባብ ጊዜ እንዳይባክን ለማድረግ፣

**ለ. የትምህርቱን አብይና ንኡስ ርዕስ ስለመወሰን**

ከትምህርት ዓላማው በመነሳት የተሳታፊዎችን ነባራዊ ሁኔታ ለመገንዘብ ያመች ዘንድ ተገቢ የሆኑ አበይትና ንኡሳን ርዕሶችን መምረጥ ያስፈልጋል::

**ሐ. አመቺ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም፣**

ለተመረጠው የትምህርት ርዕስ የሚመችና የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ ለአካባቢው አግባብነት ያለው የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በውይይት በጥያቄና መልስ፣ በፊልም ትርኢት ወይም ስርቶ በማሳየት እንደ ማለት ነው:: ስለ ትራኮማ በሽታ በሚሰጠው ትምህርት የሚሳተፉት አብዛኛዎቹ አዋቂ ሴቶችና ጎልማሶች ስለሆኑ የትምህርቱ ሂደት አሳታፊ መሆን አለበት:: ለምሳሌ የትምህርቱ መልዕክት ከአሰልጣኙ ወገን ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን ጥያቄዎችን በሚቅረብና ውይይትን በማበረታታት ሠልጣኞችን በሚገባ የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል::

### መ. የትምህርቱን ጊዜና ቦታ ስለመወሰን

ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት በተሳታፊዎች ምርጫና ፍላጎት ተስማሚ የሆነውን ጊዜና ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ትምህርቱን በቀበሌ ገበሬ ማኅበራት የስብሰባ ስፍራዎች፣ በት/ቤት፣ በጤና ኬላዎች፣ በእድሮች ስብሰባ፣ በሰንበቴ ቤት፣ በቤተ ክርስቲያናት እና በመስጊዶች እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን በግለሰቦች ቤት ጭምር መስጠት ይቻላል::

### ሠ. የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት

ስለትራኮማ በሽታ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ የተሳታፊዎችን ችሎታ በማገናዘብ በስዕላዊ መግለጫ የተደገፉ ፖስተሮች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ፍሊፕቻርቶች የመሳሰሉትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል::

### ረ. ግምገማ

የተመረጠው ርዕሰ ትምህርት መሸፈኑንና የትምህርቱ ዓላማ በአግባቡ መካተቱን እንዲሁም ተሳታፊዎች ከትምህርቱ ግንዛቤ ያገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የግምገማ ስልት መንደፍ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለመገምገም የጥያቄና መልስ ውድድር ማድረግ ወይም ስለ ትራኮማ በሽታ መሠረታዊ መረጃዎች የግምገማ ቃለ መጠይቅ ቅጽ አዘጋጅቶ በመበተንና መረጃ መሰብሰብ ጠቃሚ ነው::

ክፍል ሁለት:-

# የትራኮማ በሽታ መሠረታዊ እውነታዎች

## 2.1 ትራኮማ ምንድን ነው?

ትራኮማ ክላሚዲያ ትራኮማቲስ(Chlamydia Trachomatis) በሚባል ረቂቅ የበሽታ ተህዋስያን ምክንያት የሚመጣ፣ በሽታ ነው:: በሽታው ተስፋፍቶ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ሕመሙ በይበልጥ የሚያጠቃው ትምህርት ቤት ባልገቡና ወይም ገና ትምህርት በመጀመር ላይ ያሉ፣ በሕፃናንነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ልጆችን ነው:: በተለይም ከወንዶች ይልቅ ለሕፃናት እንክብካቤ የሚሰጡ እናቶች፣ ወጣት ልጃገረዶች፣ ሞግዚቶች፣ እህቶች፣ አክስቶችና ሴት የቤት ሰራተኞች በይበልጥ ተጠቂ ናቸው::

በአጠቃላይ ሲታይ የትራኮማ በሽታ:-

- በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት በሌለባቸው፣
- የተሟላ የጤና አገልግሎት እንደ ልብ በማይገኝባቸው፣
- የግልና የአካባቢ ንጽህና ባልተሟላባቸው፣
- የሕዝብ ብዛት በሚገኝባቸውና ድህነት ጐልቶ በሚታይባቸው አካባቢዎች ተሰራጭቶ የሚገኝ በሽታ ነው::

## 2.2 የትራኮማ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች

- ለበሽታው እንደተጋለጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ምንም ዓይነት ስሜት ወይም መለያ ምልክት ላይኖር ይችላል::
- የበሽታው ጥቃት እየተባባሰ ሲሄድ የዓይን ቆብ መቆርቆር፣ ወይም የማቃጠልና እና የመቆጥቆጥ ችግር ሊኖር ይችላል፣
- የዓይን መቅላትና ማንባት፣ ብርሃን ማየት መፍራት፣
- በላይኛው የዓይን ቆብ ውስጥ የቁስል ሽፍታ መታየት፣
- የዓይን ቆብ የቁስል ጠባሳ መፈጠር፣
- የዓይን ቅምጥ በብዛት መታየት፣
- በሽታው ስር እየሰደደ ሲሄድ የዓይን ቆብ መቆራፈድና ወደ ውስጥ የመቀልበስ ችግር (Entropion) እንዲሁም የዓይን ሽፋሽፍት የዓይን

ብርጭቆን (Cornea) መፈግፈግና ከፍተኛ የሕመም ስሜት የማስከተል ችግር ወይም ዓይነ-ጸጉር (Trichiasis) መኖር፣

➢ በመጨረሻም የዓይን ብርጭቆ በመፈግፈጉ ምክንያት የቁስል ጠባሳ ስለሚፈጠር ለአይነ ስውርነት ያጋልጣል።

*መልመጃ 1 :-*

- *ትምህርታዊ ገለጻው በስዕላዊ መግለጫ መደገፍ አለበት*
- *ከተሳታፊዎች መካከል ከተጠቀሱት ስሜቶችና መለያ ምልክቶች የሚሰማቸው ወይም የሚታይባቸው ግለሰቦች ካሉ በፈቃደኝነት እንዲገልጹ መጋበዝ ያስፈልጋል። (ለሴቶች ቅድሚያ በመስጠት ማበረታት ይገባል) በዚህ ተግባር ላይ ሴቶች እፍረት እንዳይሰማቸው አስቀድሞ በማበረታታት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።*

### 2.3 የትራኮማ በሽታ መተለላፊያ መንገዶች

➢ በዝንብ፣

➢ በዓይን ቅምጥ በተበከለ እጅ፣

➢ በተበከለ ፎጣ ወይም ማንኛውም የፊት መጥረጊያ ልብስ፣

➢ የዓይን ማዕዝ በሽታ ያለባቸው ሕፃናት ከጤነኛ ሕፃናት ጋር አብረው ሲተኙ በሚፈጠር ቀጥተኛ ንክኪ ሊተላለፍ ይችላል።

*መልመጃ 2:-*

*ከክፍሉ ውስጥ ጥቂት ተሳታፊዎችን መርጦ የትራኮማ በሽታ እንዴት ሊተላለፍ እንደሚችል ሆኖ የሚያሳይ የጨዋታ ትርኢት ማሳየት ያስፈልጋል። (በትርኢቱ ሴቶች በቅድሚያ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል።)*

## 2.4 የትራኮማ በሽታን ስርጭት የሚያባብሱ ሁኔታዎች

⇨ ድህነት፣ የሕዝብ ብዛትና በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ተፋፍጎ መኖር፣

⇨ ለዘመናት ስር ሰዶ የቆየ የተዛባ የሥራ ድርሻ፣

⇨ ህብረተሰቡ ስለ ጤናና መሠረታዊ ትምህርት ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆንና ስለበሽታው አደገኛነት በቂ ግንዛቤ ያለማግኘት፣

- ⇨ የንጹህና የበቂ ውሃ አቅርቦት ያለመኖር፣
- ⇨ በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች የግልና የአካባቢ ንጽህና ጉድለት በስፋት መታየት፣
- ⇨ የተሟላ የጤና አገልግሎት እንደ ልብ ያለመገኘት እና የመሳሰሉት ናቸው::

ለትራኮማ በሽታ መባባስ ዋና ዋና ምክንያቶች ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

**ሀ. የበቂና ንጹህ ውሃ አቅርቦት ማነስ**

በአብዛኛው በገጠርና በአንዳንድ ትናንሽ የገጠር ከተሞች በመኖሪያ ቤት አቅራቢያ ንጹህና በቂ የውሃ አቅርቦት አይገኝም:: ውሃ መቅዳት እንደ ሴቶች ብቸኛ የስራ ድርሻ ሆኖ በሚቆጠርበት አካባቢ ሴቶች በቤት ውስጥ ባለባቸው ድርብርብ የስራ ጫና ምክንያት ስለማያዳርሳቸው የውሃ አቅርቦቱ አነስተኛ ሊሆን ይችላል::

በተጨማሪ በከፍተኛ ድካም በሴቶች ጀርባ የሚመጣውን ውሃ ለመቆጠብ ሲባል ሴቶች የራሳቸውንና የልጆቻቸውን የግል ንጽህና ለመጠበቅ ቅድሚያ መስጠት አይቻላቸውም:: በመሆኑም የትራኮማ በሽታ በስፋት በመሰራጨት በይበልጥ በሴቶችና በሕፃናት ጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል::

**ለ. የግልና የአካባቢ ንጽህና ጉድለት**

የግልና የአካባቢ ንጽህና ጉድለት ለትራኮማ በሽታና ለሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ስርጭት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል:: በመሆኑም:-

- የግልና የአካባቢ ንጽህናን ለመጠበቅ አስቸጋሪ በሆነበት አካባቢ፣
- ህብረተሰቡ በብዛት በየሚዳው በሚጸዳዳበት አጋጣሚ፣
- ማንኛውም ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ በየአካባቢው በሚጣልበት ሁኔታ፣
- ማንኛውም ምግብ በተለይም እንደ ወተትና የወተት ተዋጽኦ፣ ስጋና ሌሎች ምግቦች በአግባቡ ተከድነው በማይቀመጡበት፣ እንዲሁም የምግብ ትራፊ የትም በሚጣልበት ሁኔታ፣
- ሰውና እንስሳት በአንድ ቤት ውስጥ በሚያድሩበት፣ የትራኮማ በሽታ በዝንቦች አማካይነት ከሰው ወደ ሰው የመተላለፍ እድል ከፍተኛ ነው::

### ሐ. በአንድ ቤት ውስጥ ተፋፍጐ መኖር


በአንድ ቤት ውስጥ በርካታ የቤተሰብ አባላት በአንድነት በሚኖሩበት ጊዜ በተለይም የሕፃናትን የግል ንጽህና በሚገባ ለመጠበቅ አስቸጋሪ ስለሚሆን የዝንቦች ማረፊያ እና የትራኮማ በሽታ መንስዔ ሊሆኑ ይችላሉ:: በቤተሰብ ብዛት ምክንያት ተፋፍገው በሚኖሩበት ጊዜ በተለይ እናቶችና ሴት ልጆች ትናንሽ ልጆችን አቅፈው ስለሚተኙ በሽታውን በቀጥታ ንኪኪ ሊያስተላልፉ ይችላሉ:: በዚህ ምክንያት የትራኮማ በሽታም ሆነ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የአንድ ቤተሰብ ከፍተኛ የጤና ችግር ሊሆኑ ይችላሉ::

### ሌሎች ምክንያቶች


ሴቶች በቤት ውስጥ በሚዘጋጅ እንደ ስር ኩል፣ የሻማ ጥላሸት እና ዘመናዊ ኩል እና ሌሎችም የዓይን ማስዋቢያ ነገሮችን በመጠቀም ዓይናቸው ሊቆጣ ይችላል:: ከሁሉም በላይ በአንድ የአይን ማስዋቢያ (መገልገያ) በጋራ መጠቀም የበሽታውን ስርጭት ያባብሳል:: ከዚያም በላይ በጠባብ ቤት ውስጥ እንጀራ ለመጋገርም ሆነ በሌላ ምክንያት እሳት ሲነድ ከፍተኛ ጭስ ስለሚፈጠር ሴቶች ለአይን የመቆጣት ችግር ሊጋለጡ ይችላሉ:: ዓይን በሚቆጣና በሚቆጠቁጥበት ጊዜ ሲታሽ የዓይን ማዝ አስተላላፊ ተህዋስያንን በእጅ አማካይነት ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል::

ድህነት ለትራኮማ በሽታ መሠራጨት ዋና ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል:: ምክንያቱም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖር ቤተሰብ በአነስተኛ የጎጆ ቤት ተፋፍጎ የመኖር አጋጣሚ፣ የትምህርት ዕድል ያለማግኘት፣ ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ያለመኖር እና በጤና አገልግሎት እጥረት ምክንያት ለዓይን ማዕዝ በሽታ መስፋፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል::


## 2.5. የትራኮማ በሽታ የጥቃት ደረጃዎች




የተቀለበሰ ጤናማ ዓይን (ምርመራ የሚደረግበት የላይኛው የዓይን ቆብ የውስጥ ክፍል ምልክት ተደርጎበታል)




ቀላል የዓይን መቆጥቆጥና የመቆጣት ምልክት *(Trachomatus Inflammation Folicular) TF* ይታያል::



የዓይን መቆጥቆጥና መቆጣት ምልክት
*(Trachomatus Inflammation Intense) TI*



የቁስል ጠባሳ መፈጠር ምልክት
*(Trachomatus Scaring) TS*



የዓይን የላይኛው ቆብ ጠርዝ መቆራፈድ እና ወደ ውስጥ መቀልበስ ምልክት
*Trachomatus Trichiasis TT*



የዓይን ብርጭቆ በዓይን ሽፋሽፍት መፈግፈግና ብርሃን መቀበልም ሆነ ማስተላለፍ ያለመቻል (ዓይነስውርነት) *(Corneal Opacity)*

## 2.6 የትራኮማ በሽታን ለመከላከልና ብሎም ለማጥፋት የሚያስችሉ የተቀናጁ ስልቶች

የትራኮማ በሽታ ወዲያው እንደጀመረም ሆነ ስር ከሰደደ በኋላ፣ ሊያስከትል የሚችለውን የሕመም ስቃይ ለማቃለልና አይነ ስውርነትን ለማስቀረት የሚያስችል የተቀናጀ የመከላከያ ስልት መጠቀም ወሳኝነት አለው:: እነዚህን የተቀናጁ የመከላከያና የመቆጣጠሪያ ስልቶች በቅንጅት ለመጠቀም ለአቀራረብ እንዲያመችና ለሥልጠናው አግባብነት ሲባል ቅደም ተከተሉን በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል:: ይሁን እንጂ ስልቶቹን እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በተናጥልም ሆነ በጣምራ መጠቀም ይቻላል:: እነርሱም:-

- የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ፣
- በተለይም ፊትን አዘውትሮ መታጠብና የግል ንጽህናን መጠበቅ፣
- የጸረ ተዋህሲያን የዓይን ቅባትና የሚዋጡ መድኃኒቶችን በጤና ባለሙያ መመሪያ መሠረት መጠቀም፣
- ቀላል የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና በማድረግ የትራኮማ በሽታ ሊያስከትል የሚችለውን የዓይነ ስውርነት ጠንቅ ማስወገድ ይቻላል::


### 2.6.1 የአካባቢ ንጽህናን ስለመጠበቅ

የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ የትራኮማ በሽታን በቅንጅት ለመከላከል ከሚጠቀሙት ስልቶች መካከል በግንባር ቀደም የሚጠቀስ ነው:: የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ የትራኮማ በሽታን ጨምሮ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ የትራኮማ በሽታ አስተላላፊ የሆኑ ዝንቦችን በአካባቢው እንዳይራቡ ለማድረግ ከመኖሪያ ቤት ጀምሮ እስከ መኖሪያ አካባቢ ድረስ ማንኛውንም ደረቅ ወይም ፈሳሽ ቆሻሻ፣ የሰው ዓይነ ምድር ወይም የእንስሳት እበትና አዛባ ወይም ለዝንብ መራቢያ አመቺ የሆኑ ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከአካባቢው እንዲወገዱ ማድረግ ያስፈልጋል:: በተለይም የመኖሪያ አካባቢ በሰው ሽንትና ዓይነ ምድር እንዳይበከልና የዝንብ መራቢያ እንዳይሆን ከአካባቢው ቁሳቁስ የሚሰራ የመጸዳጃ ቤት አዘጋጅቶ በንጽህና መጠቀም ይገባል::

*መልመጃ ፫:-*

- *የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅን ተግባራዊ ለማድረግ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከአካባቢው ቁሳቁስ የተገነባ፣ ንጽህናው የተጠበቀ፣ የመጸዳጃ ቤት እንዴት መስራት እንደሚቻል ሕብረተሰቡን በማሳተፍ የተግባር ልምምድ ማሳየት።*
- *በመኖሪያ አካባቢ የሚታዩ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች የዝንብ መራቢያ እንዳይሆኑ በሠልጣኞች አማካይነት ሕብረተሰቡን በማስተባበር ዘላቂና ተከታታይነት ያለው የአካባቢ የጽዳት ዘመቻ ማድረግ።*

### 2.6.2 የግል ንጽህናን ስለመጠበቅና ፊትን አዘውትሮ ስለመታጠብ



የትራኮማ በሽታንና ሌሎችንም ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ግለሰብ በነፍስ ወከፍ የግል ንጽህናን መጠበቅና በተለይም ፊትን አዘውትሮ የመታጠብን ተግባር እንደ ልማድ አድርጎ ቢወስደው የትራኮማ በሽታንም ሆነ ሌሎችን ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል፣ መቆጣጠርና ብሎም ማጥፋት ይቻላል። በተለይም ፊት መታጠብንና የግል ንጽህና አጠባበቅን ሕብረተሰቡ የእለት ተእለት ልማዱ እንዲያደርገው በተለይም በትምህርት ቤቶችና ከትምርት ቤት ውጪ ያሉ ወጣቶችን ማስተማር የባህሪ ለውጥ ሊያስገኝ ይችላል። እዚህ ላይ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ግን የግል ንጽህናን ለመጠበቅ በቂ የውሃ አቅርቦት አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ባለው አነስተኛ ውሃ የግል ንጽህናን መጠበቅና በተለይም የሕፃናትን ፊት አዘውትሮ ማጠብ የትራኮማ በሽታን ለመከላከል ጠቃሚ እርምጃ መሆኑን ከመገንዘቡ ላይ ነው። እናቶች በአነስተኛ ውሃ የሕፃናትን ፊት ማጠብ እንደሚቻል ከተገነዘቡ በሽታውን መከላከልና መቆጣጠር እንዲሁም ማጥፋት ይቻላል።


*ከልምድ እንደታየው የሕፃናትን ፊት ለማጠብ ሦስት እፍኝ ውሃ መጠቀም ይበቃል::*

*መልመጃ 4:-*

- *ስለግል ንጽህናና በተለይም የልጆችን ፊት እንዴት ማጠብ እንደሚቻል ሰርቶ በማሳየት ልምምድ ማድረግ:: (በሕፃናት የፊት አስተጣጠብ ላይ ወንዶችም እንዲሳተፉ ማድረግ)*

- *በየአካባቢው ተስማሚ የፊት መታጠቢያ መገልገያዎችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ናሙና አዘጋጅቶ ማሳየት፣ (በዚህ መልመጃ ላይ ሴቶችም ወንዶችም እኩል እንዲሳተፉ ማድረግ)*

### 2.6.3 ጸረ ተዋህሲያን የዓይን ቅባትና ሚዋጡ መድኃኒቶችን ስለመጠቀም



ለትራኮማ በሽታ ሕክምና ጸረ ተዋህሲያን መድኃኒቶችን መጠቀም በቅንጅት ከሚሰጡት የትራኮማ የመከላከያ ዘዴዎች አንዱ ነው:: ስለ ተላላፊ በሽታዎች በቂ ግንዛቤ ማግኘት ከማንኛ ውም በሽታ እራስን ለመጠበቅ እንደሚያስችል የታወቀ ነው:: ሆኖም ይህን ማሟላት በማይቻልበት ጊዜ አቅራቢያ ወደሚገኝ የጤና ድርጅት በመሄድ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ያስፈልጋል::

የትራኮማ በሽታ ለመጀመሪያ ጊዜ የልጆችንም ሆነ የአዋቂዎችን ዓይን በሚያጠቃበት ወቅት ማለትም

- የዓይን መቆጥቆጥ፣
- ማቃጠል፣ መቅላት፣
- የዓይን ቆብ እብጠት
- የዓይን ቅምጥ በዓይን ላይ መታየት ችግር ሲያጋጥም በሽታው ስር ሰዶ በዓይን ቆብ ላይ የቁስልና የቁስል ጠባሳ እንዳይፈጥር ለመከላከል ጸረ ተዋህሲያን የዓይን ጠብታ መድኃኒቶችን መጠቀም ያስፈልጋል::

ይህ የዓይን ጠብታ በዓይን ውስጥ በቀን ሁለት ጊዜ የሚጨመር ሲሆን በተከታታይ ለ6 ሳምንታት የሚሰጥ መድኃኒት ነው:: መድኃኒቱ በትራኮማ በሽታ ምክንያት

የሚከሰተውን የዓይን መቆጥቆጥና የማቃጠል የሕመም ስቃይ ለማስታገስ ፍቱን መድኃኒት ቢሆንም ህክምና ከተደረገ በኋላ ዘግይቶ ሊያገረሽ የሚችልበት አጋጣሚ ከፍተኛ ነው::

የትራኮማ ህክምናን አስመልክቶ በተደረገው ጥናት መሠረት ዚትሮማክስ (Zithromax) በመባል የሚታወቀውን የጸረ ተዋህሲያን መድኃኒት በባለሙያዎች በሚወሰን የአወሳሰድ መጠን መሠረት መውሰድ እንደ ዋና አማራጭ መጠቀም ተቀባይነት አግኝቷል:: ይህ መድኃኒት የትራኮማ በሽታ ተንሰራፍቶ በሚገኝባቸው አካባቢዎች በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ የጅምላ ሕክምና **(mass treatment)** በመስጠት በሽታው የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚረዳ ነው:: መድኃኒቱ የሚሰጥበት ዋና ዓላማ የትራኮማ በሽታ ስር እንዳይሰድና ለዓይነ ስውርነት እንዳያጋልጥ ለመከላከል ነው::

***መልመጃ 5:- ስለአይን ቅባት አጠቃቀም በተለይም ለሕፃናት የአይን ቅባት እንዴት መጨመር እንደሚቻል ለስልጠናው ተሳታፊዎች የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ማሳየት፣***

### 2.6.4 ቀላል የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና በማድረግ የትራኮማ በሽታ የሚያስከትለውን የዓይነ ስውርነት ጠንቅ ስለመከላከል

- የትራኮማ በሽታ የተለያዩ የጥቃት ደረጃዎች አሉት:: ማንኛውም ግለሰብ ለትራኮማ በሽታ በሚጋለጥበት ጊዜ በመጀመሪያ የዓይን መቆጥቆጥ፣ ማቃጠል፣ የዓይን ቆብ እብጠትና በዓይን ላይ የዓይን ቅምጥ መታየት እና የመሳሰሉት ምልክቶች ይታያሉ::

- የዓይን ሕመም ስሜቶችና መለያ ምልክቶች እንደተከሰቱ አስፈላጊው ሕክምና በወቅቱ ካልተደረገ በስተቀር የዓይን የላይኛው ቆብ ጠርዝ የውስጥ ክፍል መቁሰል፣ ጠባሳ መፈጠር፣ መቆራፈድና የአይን የላይኛው ቆብ ወደ ውስጥ የመቀልበስ ችግር ሊፈጠር ይችላል:: ይህም የዓይን ሽፋሽፍት የዓይን ብርጭቆን በተከታታይ በመፈግፈግ ለዓይነ ስውርነት ያጋልጣል:: በመሆኑም የትራኮማ በሽታ የሚያስከትለው የመጨረሻው ጠንቅ የአይነ ስውርነት ችግር ስለሆነ ይህ የአካል ጉድለት እንዳይከሰት በዓይን ቆብ ላይ ቀላል የቀዶ ሕክምና በማድረግ ችግሩን ማቃለል ይቻላል::

- በትራኮማ በሽታ ምክንያት ለዓይነ ስውርነት የሚጋለጡት ሴቶች ቁጥር ከወንዶች ይልቅ ከ2-3 እጅ የሚበልጥ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የቀዶ ህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሴቶች ቁጥር ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር አናሳ ነው።



በገጠሩ አካባቢ የትራኮማ ችግር በእጅጉ የከፋ ከመሆኑ የተነሳና የዓይን ሕክምና አገልግሎቱም ያልተስፋፋ በመሆኑ ብዙዎቹ እናቶች የዓይን ፀጉርን ለመንቀል የሚጠቀሙበትን "ወረንጦ" አንገታቸው ላይ አንጠልጥለው መሄር የተለመደ ነው።

ስለዚህ የሚከሰተውን የዓይነ ስውርነት ችግር ለማቃለል ይቻል ዘንድ ከሁሉ አስቀድሞ:-

- ስለ ዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና ዓላማና ጥቅም በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተደማጭነት ያላቸው ሴቶች፣ ወንዶችና የአካባቢው አንጋፋ ሰዎች በቅድሚያ ትምህርት እንዲሰጣቸውና ሕብረተሰቡን እንዲያሳምኑ ማድረግ።
- ሴቶች ስለ ትራኮማ በሽታ መከላከያና የሕክምና ዘዴዎች በቅድሚያ ተገቢው ስልጠና እንዲሰጣቸውና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለዖታ አቻዎቻቸው ተገቢውን የጤና መረጃ ማስተላለፍ እንዲችሉ ማድረግ።
- ሕብረተሰቡ ስር በሰደደ የትራኮማ በሽታ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የአይነ ስውርነት ችግር ለመከላከል የዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት የማግኘትን ጠቀሜታ እንዲገነዘብ ለማድረግ በተከታታይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠትና ማወያየት፣

- የትራኮማ በሽታ በህበረተሰቡ ላይ የዓይን ስውርነት ችግር በሚፈጥርበት አካባቢ በዓይን ሕክምና ባለሙያዎች አማካይነት ለትራኮማ በሽታ ጤና ተጠሪዎች በመስክ ደረጃ የቀዶ ሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ስልጠና መስጠት፣ የክትትል ስልት መዘርጋትና መደገፍ፣
- በዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና ስልጠና የወሰዱ የጤና ባለሙያዎችን በየአካባቢው መመደብ፣ መቆጣጠር፣ በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ትምህርት መስጠት፣
- እንዲሁም የቀዶ ሕክምናው አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በየወረዳው ጤና ጣቢያዎችና በአንዳንድ የገጠር ክሊኒኮች እየተሰጠ ስለሆነ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ማሳሰብ ያስፈልጋል።

LIONS - CARTER CENTER
SightFirst Initiative

የአማራ ክልላዊ መንግስት
ጤና ጥበቃ ቢሮ
Amhara Regional Health Bureau

# ማመን (SAFE)

## ትራኮማን ለመቆጣጠር ዓይነተኛ ሥልት!

**S**urgical Correction



**ማ** — የዓይን ቆብን በቀዶ ሕክምና ማስተካከል (ማስቀረጥ)

**A**ntibiotic Application



**መ** — የዓይን መድሐኒት ሳያቋርጡ መጠቀም

**F**acial Cleanliness



**ን** — የፊትን ንፅሕና መጠበቅ (ፊትን አዘውትሮ መታጠብ)

**E**nvironmental Sanitation



**ን** — የአካባቢን ንፅሕና መጠበቅ

**ስለ ትራኮማ ሲያወሱ ማመንን አይርሱ!**

**ማየት ማመን ነው!**

ክፍል ሦስት:-

## ትራኮማ: ትኩረት የሚሻ የሴቶች ጤና ችግር

### 3.1 የሴቶች ጤና አጠቃላይ ሁኔታ

የሴቶችን ጤና ጽንሰ ሃሳብ ልዩ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ:: እነዚህም ከማርገዝ፣ ከመውለድ፣ ጡት ከማጥባት፣ ህፃናትን ከማሳደግና ከመንከባከብ ጋር የተዛመዱ ናቸው:: ሴቶች ለመላው ቤተሰብ ደጋፊና ተንከባካቢ ከመሆናቸውም በላይ ወንዶችን በመስክ ሥራ በማገዝ ረገድ ግንባር ቀደም ድርሻ ስላላቸው አቅማቸው የተመናመነ ነው:: የቤተሰቡንና የማኀበረሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት ለሟሟላት በቀን ከ15-18 ሰዓት ወገብ በሚያጎብጡ ሥራዎች ላይ ተጠምደው የመዋልና የማምሸት ግዴታ ስላለባቸው የራሳቸውን ጤና ለመጠበቅ ጊዜ የላቸውም:: ሴቶች የህብረተሰቡን 50 ከመቶ በላይ የሚሆነውን የሥራ ጫና የሚሸፍኑ ቢሆንም በተዛባ የሥራ ክፍፍልና በመልካም አስተዳደር ጉድለት ምክንያት የድካማቸው ዋጋ ተጠቃሚ ሆነው አያውቁም::

የቤተሰቡንና የህብረተሰቡን ፍላጐት ለሟሟላት ሲባል ሴቶች ለረዥም ጊዜ በሥራ ተጠምደው ስለሚውሉ ከፍተኛ የጊዜ እጥረት ያጋጥማቸዋል:: ምግብ ማዘጋጀትና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት ከፍተኛ የሥራ ጫና በሴቶችና ሴት ልጆች ጫንቃ ላይ ያርፋል:: በቤተሰብ ውስጥ የምግብ እጥረት በሚፈጠርበት ጊዜ ዋናው ምግብ ለአባቶችና ለወንድ ልጆች ከተሰጠ በኋላ ከወንዶች የተረፈውን ምግብ ቀምሰው ለማደርና ለመዋል ስለሚገደዱ በምግብ ማነስና ያለመመጣጠን ችግር ምክንያት አቅማቸው ደካማ ይሆናል:: ይህ ሁኔታ በቀላሉ ለማንኛውም በሽታ ተጠቂ ሊያደርጋቸው ይችላል:: በመሆኑም ሴቶች ጊዜውና አቅሙ ስለሌላቸው የራሳቸውንም ሆነ የልጆቻቸውን ንጽህና መጠበቅ ስለሚሳናቸው እንዲሁም ለትራኮማ በሽታ ተጠቂ ለሆኑ ልጆች እለት በእለት እንክብካቤ በመስጠት ባላቸው ቅርበት ምክንያት ለትራኮማ በሽታ የተጋለጡ ናቸው::

በመሠረቱ ሴቶችን የትራኮማ በሽታን ጨምሮ ከልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች በመጠበቅ ጤናቸውን ማጎልበት ማለት የቤተሰቡን፣ የመላ ማህበረሰቡን እንዲሁም የአንድን ሃገር የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ አቅም ማጎልበት እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ በተዛባ የስራ ክፍፍል እና አመለካከት ምክንያት የሴቶች ጤንነት አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት አያውቅም:: ተሰጠ የሚባል ድጋፍ ካለ ከቅስቀሳ የዘለለ እንዳልሆነ ከነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል:: ስለሆነም ለሴቶች ሁለንተናዊ

የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግር ትኩረት ባለመሰጠቱ ዛሬም ሴቶችና ሴት ልጆች ያለአግባብ በመሰቃየት ላይ ናቸው::

| |
|---|
| *የሴቶችን አቅም ማጎልበት ልማትን ለማፋጠን ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣* |

## 3.2 የትራኮማ በሽታ የሴቶች አንገብጋቢ የጤና ችግር ነው

የትራኮማ በሽታ መላውን ህብረተሰብ የሚያጠቃ መሆኑ ቢታወቅም በተለይም ሴቶችና ሕፃናት ለምን በይበልጥ ተጠቂ ሊሆኑ እንደቻሉ የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ:: ከነዚህም መካከል የተዛባ የሥራ ድርሻ እና አመለካከት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው::

| |
|---|
| *የጤና አገልግሎት ማግኘት ሰብአዊ መብት ነው፣* |

በወንዶችና በሴቶች መካከል የሰብአዊ መብት ልዩነት ባይኖርም ከባድና የተዛባ የሥራ ድርሻ መኖር በሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ በደሎች መካከል ዋነኛው ነው:: በገጠር የሚኖሩ ሴቶች በመፍጨት፣ ውሃ በመቅዳት፣ ማገዶ በመልቀም፣ በዕረኝነት፣ ልብስ በማጠብ፣ ምግብ በማዘጋጀት፣ ለባሎቻቸውና ለወንድ ልጆቻቸው የበለጠ እንክብካቤ በመስጠት፣ አረጋውያንን በመንከባከብ፣ ሕፃናትን በማነደግ፣ ለህሙማን በቤት ውስጥ እንክብካቤ በመስጠት እና ማኀበራዊ ግዴታን ለመወጣት ቤተሰቡን በመወከል በቀን ከ15-18 ሰዓታት በሚፈጁ ሥራዎች ቀንና ሌሊት ተጠምደው ያለእረፍት ሲለፉ ይታያሉ:: በግብርና ሥራም ቢሆን ሴቶች በእርሻ፣ በጎልጎሎ፣ በአጨዳ፣ የሚሰማሩ ከመሆኑም በላይ የገበሬውንና የቤተሰቡን ምሳና እራት በማዘጋጀት የተጠመዱ ናቸው::

ይሁን እንጂ በመስክም ሆነ በቤት ውስጥ የሚያደርጉት የስራ አስተዋጽኦ እውቅና የማይሰጠውና በገንዘብ የማይተመን በመሆኑ አምራችነታቸው የሚያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ከግምት ውስጥ ገብቶ አያውቅም:: ይህም በሴቶች ላይ ከፍተኛ የዝቅተኝነትና የጥገኝነት ስሜት በማሳደሩ ሕልውናቸውን እየተፈታተነ ይገኛል:: ሴት ልጆቻቸውም ለዚሁ ችግር የተጋለጡ ስለሆኑ ወደፊት ሁኔታው እንዳይባባስ የሴቶችን መብት በማስጠበቁ ረገድ ተገቢው ትምህርት ሊሰጥ ይገባል::

በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ደግሞ በቂ ዕውቀትና ገንዘብ ስለሌላቸው በአብዛኛው የሚሰማሩት ትርፍ በማያመጡ እንደ አነስተኛ የባልትና ሱቅ፣ እንጀራ ጋግሮ መሸጥ፣ መሸታ ቤት መክፈት፣ በጉልት የገበያ ንግድና በመሳሰሉት አነስተኛ ሥራዎች ላይ ነው:: ከዚህም ባሻገር ወጣት ሴቶች ከገጠር ወደ ከተማ በመኮብለል ለሴተኛ አዳሪነት በመዳረግ፣ ለተለያዩ ደባል ሱሶች በመጋለጥ፣ የሚወልዱዋቸውን ልጆች ብቻቸውን በጎዳና ላይ በማሳደግና በመንገላታት ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል::

በአጠቃላይ ሴቶች:-

- ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አቋማቸው ዝቅተኛ እንዲሆን የሚያደርግ ተጽዕኖ በመኖሩ፣
- የውሃ አጠቃቀምና አቅርቦት፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ፣ የመኖሪያ ቤቶች ንጽህና አጠባበቅና አያያዝ የመሳሰሉት ሙሉ በሙሉ የሴቶች የሥራ ድርሻ መደረጉ ፣
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዓይነ ስውርነት ከተጋለጡት 6 ሚሊዮን ሕዝቦች መካከል 75 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው ስለሚታወቅ::
- በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከሚኖሩ አባቶችና ወንድሞች ይልቅ በዓይነ ጸጉር (Trichiasis) የሚሰቃዩት 70% የሚሆኑት እናቶችና ሴት ልጆቻቸው 30 በመቶ የሚሆኑት አባቶችና ወንድ ልጆች መሆኑ ስለሚታወቅ፣
- በትራኮማ በሽታ ከሚጠቁ 4 ሰዎች መካከል 3ቱ ሴቶች መሆናቸው እና በመሳሰሉት ምክንያት በትራኮማ በሽታ የሴቶች አንገብጋቢ የጤና ችግር ሊሆን ችሏል:: ይህ አብይ ችግር በሴቶች ቀጥተኛ ተሳትፎና በወንዶች ጠንካራ ድጋፍ ሊወገድ የሚገባው ነው::

*«የትራኮማ በሽታ ለዘመናት የሴቶች አንገብጋቢ የጤና ችግር ሆኖ የቆየ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ተገቢው የቁጥጥር፣ የመከላከልና የሕክምና እርምጃ አልተወሰደም::»*

***መልመጃ 6:-***

***የትራኮማ በሽታ ለምን የሴቶች አንገብጋቢ የጤና ችግር ሊሆን እንደቻለ ተሳታፊዎችን በቡድን መድቦ የውይይትና የክርክር መድረክ በመፍጠር የተሳታፊዎችንና የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት::***

### 3.3 በተዛባ የስራ ክፍፍል ምክንያት የሴቶች ለትራኮማ በሽታ የመጋለጥ አጋጣሚ

ከበርካታ ጥናታዊ ዘገባዎች በተገኘው መረጃ መሠረት የትራኮማ በሽታ ከወንዶቹ ይልቅ ሴቶችን በይበልጥ እንደሚያጠቃ ታውቋል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት ልጆች ግንባር ቀደም ተጠቂ በመሆናቸው እናቶች ባላቸው ቅርበት ምክንያት የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው:: ስለዚህ ሴቶች ባለባቸው ተደራራቢ የሥራ ጫና ምክንያት የራሳቸውንም ሆነ የልጆችን ንጽህና ለመጠበቅ ስለሚሳናቸው ከወንዶቹ ይልቅ በሴቶች ላይ ጎልቶ ይታያል::

1. **ለሕፃናት እንክብካቤ በመስጠት:-** ሴቶች ከወንዶች የበለጠ በከፍተኛ ደረጃ የሚጋለጡበት ዋናው ምክንያት የትራኮማ በሽታ ተጠቂ ለሆኑ ህፃናት አሣዳጊና ተንከባካቢ በመሆናቸው ነው::

2. **የውሃ አጠቃቀምና አቅርቦት:-** የውሃ እጥረት የሚያስከትለው ዘርፈ ብዙ የጤና ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ ውሃ እንደ ልብ በማይገኝበት ሁኔታ የግል ንጽህናንና በተለይም የሕፃናትን ፊት የማጠብ አጋጣሚ እየቀነሰ ይሄዳል:: ይህ ሊሆን የሚችለው በከፍተኛ ድካም በሴቶች ጀርባ የሚመጣውን ውድ ውሃ ለመደበኛ የንጽህና አገልግሎት በተለይም ፊትን ለመታጠብ እንዳይውል ለመቆጠብ በሚፈጸም ድርጊት ነው:: ይሁን እንጂ በመስክ የተደረጉ የሙከራ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በተገኘው አነስተኛ ውሃ ፊትን መታጠብ የትራኮማ በሽታን ለመከላከል እንደሚቻል ለማወቅ ተችሏል::

3. **የሴቶች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን:-** የሴቶች ማኅበራዊና የኢኮኖሚ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን በቀላሉ ለትራኮማ በሽታ መጋለጥ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል:: በተለይም ሴቶች ስለጤና አጠባበቅ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በሆነ ቁጥር ችግሩ የተባባሰ ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም የሴቶች የትምህርት ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር ግንዛቤያቸው እየጐለበተ ስለሚመጣ የራሳቸውንም ሆነ የልጆችን የግል ንጽህና ለመጠበቅ ብቃትና ትጋት ስለሚኖራቸው በትራኮማ በሽታ የመጠቃት አጋጣሚው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል::

4. **የአካባቢ ንጽህና ጉድለት:-** የአካባቢ ንጽሕና ጉድለት ለትራኮማ በሽታ መባባስ ዋና ምክንያት ነው:: የእያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ የመፀዳጃ ቤት ባለቤትና ተጠቃሚ መሆን እንዲሁም ሰዎች ከእንስሳት ጋር ያላቸው ቅርበት እና ለማዳበሪያ

እና ለማገዶ እበትን በየአካባቢው እየጠፈጠፉ መጠቀም፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ ያለማስወገድ፣ በየሜዳው መጸዳዳትና የመሳሰሉት ድርጊቶች አካባቢን ስለሚበክል የትራኮማ በሽታን ጨምሮ ለበርካታ ተላላፊ በሽታዎች የመጋለጥ አጋጣሚ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል::

5. **የመኖሪያ ቤት አካባቢ ጥበትና የንጽህና ጉድለት:-** የመኖሪያ ቤት አካባቢ የንጽህና መጓደል ለትራኮማ በሽታ ያጋልጣል:: አንዳንድ ጥናታዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የበርካታ ሰዎች ተፋፍጎ መኖር ለትራኮማ በሽታ የመጋለጥን ዕድል ይጨምራል:: ምንም መስኮትና የአየር መውጫና መግቢያ በሌለው ቤት ውስጥ እንጀራ የሚጋግሩና ሌሎች ምግቦችን የሚያዘጋጁ ወይም ምግብ በሚበስልበት ቤት ውስጥ የሚተኙ ሕፃናት በከፍተኛ ደረጃ ለትራኮማ በሽታ የተጋለጡ ናቸው:: በቤት ጥበትና የንጽህና ጉድለት ምክንያት ሴቶች ዓይናቸው በጪስ ስለሚጐዳ ለዓይን መቆጣትና ለትራኮማ በሽታ በይበልጥ ተጠቂ ይሆናሉ:: ይሁን እና ጪስ ለትራኮማ በሽታ የመጋለጥን አጋጣሚ ይጨምራል እንጂ መንስኤ ሊሆን እንደማይችል ከወዲሁ መገንዘብ ይገባል::

***የሴቶችን አቅም ለማጎልበት የተሟላ ጤና አገልግሎት መስጠት ወሳኝ ነው፣***


## 3.4 የትራኮማ በሽታ በሴቶች ላይ የሚያስከትለው ጫና


ትራኮማ በህብረተሰቡ ላይ የጤና መታወክ፣ የህመም ስቃይና የአካል ጉድለት የሚያስከትል በሽታ ነው:: በሽታው መላውን ህብረተሰብ የሚያጠቃ ቢሆንም በተለይም በሕጻናትና በሴቶች ላይ የሚያስከትለው ጫና ከፍተኛ ነው:: ትራኮማ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በአጠቃላይ በታዳጊው ክፍለ ዓለም በተለይም ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሳሕራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች እጅግ በጣም ተንሰራፍቶ ይገኛል::

በትራኮማ በሽታ ምክንያት የሚከሰተው ዓይነ ስውርነት በሰዎች ላይ የሚያስከትለውን የዕድሜ ብክነት (Disability Adjusted Life years-DLY) ለማወቅ በ1982 (1990) ዓ.ም ዓለም አቀፋዊ ጥናት ተካሂዶ ነበር:: በመሆኑም በዓይነ ስውርነት ምክንያት የዕድሜ ብክነት ከደረሰባቸው 3,298 ሰዎች መካከል 2,370 የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው ታውቋል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 71.9% መሆኑ ነው:: በዚሁ ጥናት ውስጥ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሳሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሃገሮች ላይ ዓይነ ስውርነት እያደረሰ ያለውን የእድሜ ብክነት ለማወቅ በተደረገው ጥናት ከታቀፉት 901 ሰዎች መካከል 690 የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ ይህም በሴቶች ላይ የደረሰው የእድሜ ብክነት 76.6% መሆኑን

ያመለክታል:: ስለዚህ ይህ ጥናት ሴቶች በዓይነ ስውርነት ምክንያት የሚከሰተው የዕድሜ ብክነት ችግር ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው::


በሀገራችን በተለይም በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትራኮማ በሽታን የስርጭት መጠን ለማወቅ በአራት ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 15 ወረዳዎች እድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች በሆኑ ልጆች እና ከ39 ዓመት በላይ በሆኑ ሴቶች ላይ በተደረገው ጥናት የተገኘውን ውጤት በሚከተሉት ቀመሮች ወይም ግራፎች ይመልከቱ::


የዓይነ-ፀጉር /ትሪኪያሲስ/ ሥርጭት በእድሜና በፆታ
ጥቅምት 1996 ዓ.ም.
ሴት
ወንድ
የሥርጭት መጠን (%)
30
25
20
15
10
5
0
0 - 4
5-9
10-14
15-19
20-24
25-29
30-34
35-39
40-44
45-49
50-54
55-59
60-64
65-69
>=70
የእድሜ ክልል



የትራኮማ በሽታ ሥርጭት እድሜያቸው ከ 1 እስከ 9 ባሉ ልጆች
ጥቅምት 1996 ዓ.ም.
የሥርጭት መጠን (%)
100
90
80
70
60
50
40
30
20
10
0
ደ/ታቦር
ፋርጣ
ፎገራ
ላ/ጋይንት
ታ/ጋይንት
ሊቦ ከምከም
ጎ/ዙሪያ
ምስ/በለሳ
ምዕ/በለሳ
ሁለተኛ
ጎንቻሲሶ
እነብሴ
ባ/ዙሪያ
ጃቢ ጠህናን
ደልማናዶ.
ወረዳዎች

## 3.5 የሴቶች ዓይነ ስውርነት የሚያስከትለው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ



ሴቶች ባላቸው መጠነ ሰፊ የስራ ድርሻ ምክንያት ለአንድ ቤተሰብና ህብረተሰብ የሚሰጡት የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ድጋፍ እንዲሁም የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው:: በትራኮማ በሽታ ምክንያት በሴቶች ላይ የሚከሰተው ማንኛውም ችግር የሚጎዳው ሴቶችን ብቻ ሳይሆን በመላው ቤተሰብና ሕብረተሰብ የማህበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ አቋም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያስከትላል::

ሴቶች ለድካማቸው ምንም ዋጋ ሳይሰጠው በየዕለቱ የሚያከናውኑት ስራ ማለትም ለቤተሰብ እንክብካቤ መስጠት፣ ውሃ መቅዳት፣ እንጨት መልቀም፣ ልብስ ማጠብ፣ ምግብ ማዘጋጀት፣ ከብቶችን ማሰማራት፣ እርሻና ሌሎች መደበኛ ስራዎች ይቋረጣሉ:: በዚህ ረገድ በአጠቃላይ እያንዳንዱ ቤተሰብና ማኅበረሰብ አምራች የሆነውን ጠንካራ የሰው ኃይል የሚያጣ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ሴቶች ደግሞ ዓይነ ስውር በመሆናቸው ምክንያት ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ ሴቶች የስራ እድላቸውን ስለሚያጡ የትራኮማ በሽታ የኢኮኖሚ አቅማቸውን በማዳከም ለጥገኝነት ይዳረጋሉ:: ለጾታዊ ጥቃትም እጅግ በጣም ይጋለጣሉ::

ከዚህ በተጨማሪ በዓይነ ስውር ሰዎች ላይ ለአደጋ የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው:: ከዓይናማዎቹ ጋር ሲነጻጸር በእርግጥ በአፍሪካ የሚኖሩ ዓይነ ስውር የሆኑ ሰዎች አምራች በሆኑበት የአፍላ የዕድሜ ክልል ውስጥ የመሞታቸው አጋጣሚ በሦስት እጥፍ ያደገ ነው::

## 3.6 የሴቶች ዓይነ ስውርነት በቤተሰብ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ

ዓይነ ስውርነት በአንድ ቤተሰብ ወይም ማኅበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ነው:: እናቶች ለአይነ ስውርነት ሲጋለጡ ሴት ልጆቻቸው በመተካት ቤተሰቡን የማስተዳደር ግዴታ ይጣልባቸዋል:: ያለእድሜያቸው የሚረከቡት የቤተሰብ ኃላፊነት የሚያስከትልባቸው ጫና እንደተጠበቀ ሆኖ ትምህርታቸውን

ለማቋረጥ ይገደዳሉ:: ያለ አቅማቸው ምግብ ለማብሰል፣ ውሃ ለመቅዳት፣ ማገዶ ለመልቀምና በመሳሰሉት ከባድ ሥራዎች የሚጠመዱ ከመሆኑም በላይ የእናቶቻቸውን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት የሚያደርጉት እንክብካቤ ተጨማሪ ጊዜ ይጠይቃል:: የአካል ጉድለት ካለባቸው ቤተሰቦች የሚወለዱ ሴት ልጆች እጮኛ የማግኘት እድላቸው ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ አጋጣሚው እንኳን ቢገኝ አይነ ስውር እናት ያላት ሴት ልጅ ለእናቷ ለበርካታ ዓመታት እንክብካቤ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ሊሰጣት የሚገባው ጥሎሽ ሆን ተብሎ ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል ከነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል::

የአንዲት ሴት ለአይነ ስውርነት መጋለጥ የቤተሰቡን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ የሚያጨልም ስለሆነ የቤተሰቡ አስተዳደር በመናጋት ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ቀውስ ይጋለጣል:: ከዚያም በላይ በ40ዎቹና በ50ዎቹ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በ20ዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች በዚህ በአፍላ እድሜያቸው በትራኮማ በሽታ ምክንያት በሚከሰተው ዓይነ ስውርነት ጎዳና ተዳዳሪ በመሆን በልመና ሥራ ላይ የሚሰማሩ ስለሆነ ይህም የአንድን ሀገር አምራች የሰው ኃይል ከመቀነሱም በላይ ጎዳና የሚወለዱትንም ሕፃናት ቁጥር ይጨምራል፣ ለጉስቁልና የተጋለጡ ዜጎች ይበረክታሉ::

*የትራኮማ በሽታ የሚያስከትለው ተጽእኖ መላውን ቤተሰብ የሚጎዳ ቢሆንም የእናቶች ለዓይነ ስውርነት መጋለጥ በሴት ልጆች ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ የከፋ ነው::*

## 3.7 በትራኮማ ሕክምና ላይ የሚደረግ የባህልና የፆታ ተጽዕኖ

አባታዊ ሥርዓት (patriarchy) በሚንጸባረቅባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ሴቶች ያለባቸውን የጤና ችግር መናገር እንደ ነውር ስለሚቆጠር ችግራቸውን ከመግለጽ ይቆጠባሉ:: በዚህም ምክንያት ሴቶች ትራኮማ ሲይዛቸው በምስጢር ጠብቀው ስለሚያቆዩ ችግሩ የሚታወቀው ለዓይነ ስውርነት ከተጋለጡ በኋላ ወይም ወደዚያው ሲቃረቡ ነው::

በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ ሴቶች አዘውትረው አመመኝ፣ ደከመኝ ብሎ መናገር እንደ ጨዋ ሴት ባህሪ አይቆጠርም:: በባሎቻቸውና በጓደኞቻቸው እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ እራስ ወዳድና ሰነፍ ያስቆጥራል ብለው ስለሚሰጉ አመመኝ ብሎ መናገር የተለመደ አይደለም:: አዘውትረው ስለራሳቸው የጤና ችግር የሚያወሩ ሴቶች አሳዳጊ የበደላቸው፣ ሰነፍና የሙያ ብቃት የሌላቸው፣ ሊወጡት የሚገባቸውን የቤተሰብ ክብካቤና የምግብ ዝግጅት ለመወጣት ብቃት የሌላቸው ሆነው እንዳይታዩ ይፈራሉ::

በዓይን ጸጉር (Trichiasis) የሚሰቃዩ ቢሆኑም እንኳን ሥራቸውን ከመስራት በስተቀር የሕክምና ዕርዳታ የማግኘት ፍላጐት የላቸውም::

በሌላው ወገን ደግሞ በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ሴቶች አዘውትረው ፊትን መታጠብና ከሌሎቹ የበለጠ የግል ንጽህናቸውን ጠብቀው ሲታዩ እንደ መሽቀርቀር ስለሚቆጠር ይህ ዓይነቱን ባህላዊ ተጽዕኖ በመፍራት አዘውትረው ፊታቸውን ከመታጠብ ሊቆጠቡ ይችላሉ:: ስለዚህ ስለራሳቸው የጤና ችግር የሚያወሩ ሴቶች ስለትራኮማ በሽታ መንስኤ የተለያዩ እምነቶች በሚሠጡበት አካባቢ ጊዜው ስለሌላቸው ስለበሽታው ምንነት አስፈላጊውን ትምህርት ለማግኘትና ግንዛቤያቸውን ለማዳበር አይችሉም::

ስለ ትራኮማ በሽታ ግንዛቤ በሌለው ማኀበረሰብ አመለካከት የዓይነ ስውርነት መንስዔ ናቸው ተብለው የሚሰጡ ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ በአንዳንድ አካባቢዎች ዓይነ ስውርነት ከቀናተኛ ሰው ጋር በድንገት አይን ለአይን ከመተያየት የተነሳ ሊከሰት እንደሚችል ይታመናል:: ትራኮማ ለጭስ በመጋለጥና አዘውትረው በማልቀስ ምክንያት እንደሚመጣም ያምናሉ:: ይህ ግን ከእውነት የራቀ ነው:: ምክንያቱም አዘውትሮ ለጭስ መጋለጥና ማልቀስ የትራኮማ በሽታን ለማስተላለፍ አመቺን ሁኔታን ከመፍጠር አልፎ የበሽታው መንስዔ ሊሆኑ አይችሉም:: በሽታው በእርጅና ምክንያት ሊመጣ እንደሚችል አብዛኞቹ ያምናሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ስለ ትራኮማ በሽታ በተናገሩ ወይም በተወያዩ ቁጥር በሽታው ስር እየሰደደ ለጉዳት እንደሚያጋልጥ በማመን ስለትራኮማ በሽታ ማውራት የሚከለከልበት አጋጣሚ በርካታ ነው:: እንዲያውም ይህ ዓይነቱ ድርጊት የአምላክን ሥልጣን እንደ መፈታተን ይቆጠራል የሚል ስጋት ያላቸው ወገኖች ጥቂት አይደሉም:: የትራኮማ በሽታን የግልና የአካባቢ ንጽህናን በመጠበቅ መከላከል እና ዓይነስውርነትን ማስቀረት የሚቻል መሆኑ እየታወቀ ሰዎች በኋላ ቀር አመለካከት ምክንያት ስለበሽታው ከመናገር መቆጠብ ወይም ንቆ የመተው ሁኔታ እየተባባሰ እንዲሄድ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ቀስ በቀስ ለዓይነ ስውርነት ያጋልጣል::

ስለዚህ ስለ ትራኮማ በሽታ መሠረታዊ እውነታዎች ለመላው ህብረተሰብ በተለይም የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ሴቶች በየአካባቢውና በየአጋጣሚው የባህሪ ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው::

ክፍል አራት:-

## ትምህርቱ ሊያካትታቸው የሚገባ ዋና ዋና ርዕሶች

ትራኮማንና በየአካባቢው የህብረተሰቡ አንገብጋቢ የጤና ችግሮች የሆኑ ሌሎችንም ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ:-

- ስለንጹህና በቂ የውሃ አቅርቦት፣
- ስለደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣
- በራሪ ነፍሳትን ስለመከላከል፣
- ስለመጸዳጃ ቤት አስፈላጊነት፣
- ለጤና ተስማሚ የሆነ የመኖሪያ ቤት አሰራር እና የመሳሰሉትን ክፍለ ትምህርቶች መዳሰስ ያስፈልጋል::

### 4.1 ስለ ንጹህና በቂ የውኃ አቅርቦት

- ለመጠጥና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውለው ውሃ በተፈጥሮ የሚገኘው ከዝናብ፣ ከምንጭ፣ ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከኩሬና ከሃይቅ ነው:: ህይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ለመኖር ከአየር ቀጥሎ ውሃና ምግብ ያስፈልጉታል:: የውሃ ተፈላጊነት ከፍተኛ ቢሆንም በተለይም ለመጠጥ፣ ለምግብ ዝግጅትና ለመታጠቢያ የምንጠቀምበት ውሃ ንጽህናው ካልተጠበቀና ብርቱ ጥንቃቄ ካልተደረገለት በስተቀር በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው::

- ውሃ ለመጠጥ አገልግሎት ተስማሚ ነው የሚባለው በበሽታ አምጪ ተህዋሲያን ያልተበከለ፣ ከመርዛማ ንጥረ ነገሮች ነፃ የሆነ፣ መጥፎ ጠረንና ቀለም የሌለው፣ ከተወሰነው መጠን በላይ/በታች ማዕድኖች የሌለው፣ ልዩ ጣዕምና ድፍርስነት የሌለው ሆኖ ሲገኝ ነው:: ለምሳሌ የውሃ ጉድጓድ ካልተከደነና ዙሪያው ካልታጠረ በስተቀር ውኃ በቀላሉ ስለሚበከል ውሃ ወለድ በሽታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ:: ስለዚህ ሰዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠቀሙበትን ውሃ ለጤና ጠንቅ ከሆኑ ተህዋሲያንና ትላትሎች፣ እንዲሁም ከመርዛማና ሌሎች ጎጂ ንጥረ ነገሮች ነፃ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

- በውሃ ብክለት ምክንያት የሚከሰቱ በርካታ ውሃ ወለድ ተላላፊ በሽታዎች አሉ:: የተበከለ ውሃ መጠጣት እንደ አሜባ፣ ኮሌራ ተቅማጥና የደም ተቅማጥ የመሳሰሉት በሽታዎች ሊያስከትል ይችላል:: በውሃ እጥረት ምክንያት የግል ንጽህናን መጠበቅ ሳይቻል ሲቀር እንደ እከክ፣ የሆድ ጥገኛ ትሎች፣ ተሰቦና የትራኮማ በሽታዎች ይከሰታሉ:: በውሃ ውስጥ በሚኖሩ የበሽታ አስተላላፊ ነፍሳት አማካይነት እንደ ቢልሃርዚያ፣ የአፍንጫና የጆሮ ቁስል በሽታዎች ሕብረተሰቡን ያጠቃሉ::

በውሃ ላይ ወይም በአካባቢው በሚራቡ ነፍሳት አማካይነት እንደ ወባ፣ ቢጫ ወባና ሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የጤና ቀውስና የሞት አደጋ እንደሚያስከትሉ የታወቀ ነው::

ስለዚህ የንጹህና በቂ የውሃ አቅርቦት መኖር ለመጠጥና ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለልብስ ማጠቢያና ለግል ንጽህና መጠበቂያ እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚሰጠው ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ በአጠቃላይ የግል ንጽህናን ለመጠበቅ፣ በተለይም የሕፃናትን ፊት አዘውትሮ በማጠብ ለዝንብ እንዳይጋለጡ ለማድረግና የትራኮማ በሽታን ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር ወሳኝነት አለው::

በመሆኑም ይህንን አብይ የኅብረተሰብ ችግር ለማቃለል የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ ከተቻለ በመኖሪያ ቤቶች አቅራቢያ የውሃ መገኛ ምንጮች እንዲኖሩ ማድረግ፣ የውሃ አቅርቦትና አጠቃቀም እንደ የሴቶች ብቸኛ የስራ ድርሻ መታየቱ ቀርቶ ወንዶችም ውሃን በመቅዳትና በቁጠባ በመጠቀም የሕፃናትን የግል ንጽህና ለመጠበቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን ትምህርት መስጠትና የማኅበረሰቡን አመለካከት መለወጥ ያስፈልጋል::

## 4.2 የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

ከድርጅቶች፣ ከመኖሪያ ቤቶችና አካባቢዎች የሚፈጠሩት ቆሻሻዎች ደረቅ ወይም ፍሳሽ ቆሻሻ በመባል ይታወቃሉ:: ደረቅ ቆሻሻ የሚባሉት ጠጣርና ከፊል ጠጣር የሆኑ ከምግብም ሆነ ከሌሎች የወዳደቁና የሚሰበሰቡ ለምሳሌ እንደ አመድ፣ የመንገድ ጥራጊ፣ የሞቱ እንስሳት፣የተጣሉ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ የምግብ ትራፊዎችን ያጠቃልላል::

ፍሳሽ ቆሻሻ የሚባለው ደግሞ የሰው ሽንትና ዓይነ ምድር፣ የከብት እበትና አዛባ እንዲሁም ከመኖሪያ ቤት የሚወጡ ልዩ ልዩ እጣቢዎችን ያጠቃልላል:: ደረቅም ሆነ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በአግባቡ ካልተወገዱ በስተቀር የዝንብና የሌሎችም ልዩ ልዩ በራሪ ነፍሳት መራቢያ ይሆናሉ:: በተለይ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ማስወገጃ፣ መቅበሪያ ወይም ማቃጠያ በሌለበት ሁኔታ እንደ ዝንብ በመሳሰሉ በራሪ ነፍሳት አማካይነት እንደ ትራኮማ እና ሌሎችም የአንጀት ተውሳኮች ህብረተሰቡን ሊያጠቁት ይችላሉ::

ስለዚህ በማንኛውም ደረቅም ሆነ ፈሳሽ ቆሻሻ ምክንያት አካባቢ እንዳይበከልና ኅብረተሰቡ በትራኮማም ሆነ በሌሎች ተላላፊ በሽታዎች እንዳይጠቃ በተለይም የሰው ሽንትና አይነምድር በመኖሪያ ግቢ ውስጥ የመጸዳጃ ቤት በማዘጋጀትና በአግባቡ በመጠቀም እንዲወገድ ማድረግ፣ የከብት እበትና እንዲሁም ከቤትና ግቢ ውስጥ የሚወጡ ደረቅ ቆሻሻዎች ከመኖሪያ ቤት ርቀው እንዲወገዱ፣ በተለይም ደረቅ ቆሻሻዎች እንዲቃጠሉ፣ አስፈላጊም ሲሆን ጉድጓድ ውስጥ በመድፋትና በመቅበር ለዝንብና ለሌሎች በራሪ ነፍሳት ማረፊያና መራቢያ እንዳይሆን ማድረግ ያስፈልጋል::

በተለይም በገጠር ደረጃ :- ከቤት ውስጥና ከግቢ የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለማከማቸትና ለማስወገድ የሚረዳ ጉድጓድ እንደ አመችነቱ ከመኖሪያ ቤት ቢያንስ 50 ሜትር (100 ክንድ) ርቆ በመቆፈር፣ ዕለት ተዕለት ሊቃጠሉ የሚችሉትን ደረቅ ቆሻሻዎች አጠራቅሞ በማቃጠል፣ አመዱን በማውጣት ወደ አትክልት ውስጥ ከበተኑ በኋላ ጉድጓዱን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል:: ከዚህ በተረፈ ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ በየአካባቢው በሚገኙ ጎድጓዳ ስፍራዎችን በመሙላት ወደ ሜዳማነት ለመለወጥ የሚያስችል እርምጃ መወሰድ አለበት::

**የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አመራረጥን በተመለከተ:-**

- ተዳፋትነት ያለው ሆኖ ከህብረተሰቡ መኖሪያ ሠፈርና ክልል ውጭ ቢያንስ ከ1 ኪ.ሜ ያላነሰ ርቀት ባለው ስፍራ የአካባቢን ውሃ በማይበክልበት ሁኔታ ማስወገድ::
- ማንኛውም የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለመጠጥም ሆነ ለሌላ አገልግሎት ልንጠቀምባቸው ከሚችሉ የውሃ መገኛ አካላት በስተግርጌ መሆን አለበት፣
- በግል ወይም በመኖሪያ አካባቢ ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ የምንጠቀምበት ቦታ በአካባቢ ከሚገኝ የውሃ መገኛ በ30 ሜትር እርቀት ወይም በስተግርጌ መሆን ይገባዋል፣
- ደረቅ ቆሻሻን በመቅበር የምናስወግድበት አካባቢ ለዝንብና ለሌሎችም በራሪ ነፍሳት መራቢያ አመቺ እንዳይሆን ቆሻሻው ከተጣለ በኋላ በሚገባ አፈር መልበስ አለበት፣

- ደረቅ ቆሻሻን በማቃጠል የምናስወግድበት አካባቢ የእሳት አደጋ እንዳያስከትል ከመኖሪያና በቀላሉ እሳት ከሚያስነሱ ቦታዎች የራቀ መሆን አለበት፡፡

**የፍሣሽ ቆሻሻ ምንጭ**

ፍሣሽ ቆሻሻ እንደ ምንጩ የሚለያይ ቢሆንም በዓይነቱ ከሰው ሽንትና ዓይነ ምድር እንዲሁም ከቤት እጣቢ የሚወጣ ሊሆን ይችላል፡፡ በጎርፍ አማካይነት የሚከሰት ፍሣሽ ቆሻሻ ዝናብ ከዘነበ በኋላ በመሬት ላይ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ በማግበስበስ የሚከሰት የፍሳሽ ዓይነት ነው፡፡

ፍሣሽ ቆሻሻ ከሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች መካከል፡-

- መጥፎ ሽታ በመፍጠር ሰዎች ለጉንፋንና ለመሳሰሉት በሽታዎች እንዲጋለጡ ያደርጋል፣
- የመኖሪያ አካባቢ ውበትን ይቀንሳል፣
- ለዝንቦች መራቢያ በመሆን እንደ ትራኮማ፣ የአንጀት ተውሳኮች ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

ስለዚህ የደረቅም ሆነ የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ አጠባበቅና አወጋገድ ህብረተሰቡ ለትራኮማና ለሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች የማያጋልጥ መሆኑን እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ቤተሰብ እና ህብረተሰብ ማወቅና መገንዘብ ይገባዋል፡፡

## 4.3 የበራሪ ነፍሳትና ቆርጣሚ እንስሳት ቁጥጥር

ማንኛውም ተላላፊ በሽታ ከሰው ወደ ሰው ወይንም ከሌሎች የበሽታ አምጪዎች ወደ ሰው ሊተላለፍ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ በበሽታ አስተላላፊ ነፍሳት፣ ተባዮች፣ ተናዳፊዎችና በቆርጣሚ እንስሳት አማካይነት ነው፡፡ የትምህርታችን ዋናው ርዕስ ጉዳይ የትራኮማ በሽታ አስተላላፊ ዝንቦች ላይ የሚያተኩር ቢሆንም በተለይ ለገጠሩ ማኀበረሰብ ሁለ ገብ ትምህርት መስጠት ይቻል ዘንድ በተለይም እንደ ዝንብና ስለ አንዳንድ በራሪ ነፍሳት፣ ተባዮች፣ መሠረታዊ መረጃ ባጭሩ መዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡

በራሪ ነፍሳት የሚባሉት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው በርረው በቀላሉ ሊደርሱ የሚችሉ ነፍሳት ናቸው፡፡ በማንኛውም ቆሻሻ ላይ አርፈው ፈጥነው ወደ ቤት በመግባት በምግብና

ዕቃዎች ላይ በማረፍና በሽታን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ የጎላ ሚና ያላቸው ዝንብና ትንኝ ናቸው::

ተባዮች የምንላቸው አብዛኛውን ጊዜ ደም በመምጠጥ የሚኖሩ ቅማልና ቅጫም፣ ቁንጫ፣ ትኋን እንዲሁም ሙጀሌ የመሳሰሉት ነፍሣት ናቸው:: እነዚህ ተባዮች እንደተስቦ፣ የቆዳ ማሳከክ እና ልዩ ልዩ የጤና ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ:: ስለዚህ ህብረተሰቡ የግልና የአካባቢ ንጽህናን በመጠበቅ እንደ አይጥ የመሳሰሉትን ቆርጣሚዎች በማጥፋት ሊከላከላቸው ይችላል::

ተናዳፊ ነፍሳት የሚባሉት እንደ እባብ፣ ጊንጥ ያሉት ሲሆኑ በአብዛኛው የሚገኙት በወይናደጋና በቆላማ አካባቢዎች ነው:: ለእነዚህ አደገኛ ነፍሳት መነደፍ እስከሞት አደጋ ሊያደርስ ይችላል:: በመሆኑም የአካባቢ ንጽህናን በመጠበቅ እነዚህን አደገኛ ተናዳፊ ነፍሳት መከላከል ይቻላል:: በቤት ዙሪያ የሚበቅለውን ሳርና ጥሻ በየጊዜው ማጨድና መመንጠር ቆሻሻ ጉድጓድ ውስጥ መጣልና ማቃጠል ተናዳፊ እንስሳትን ይከላከላል::

ትንኞች ወባና ቢጫ ወባ የተባሉ አደገኛ የሆኑ በሽታዎችን የሚያስተላልፉ በራሪ ነፍሳት ናቸው:: ስለዚህ ህብረተሰቡ ትንኞችም ጠላቱ መሆናቸውን አውቆ ወባንና ሌሎችንም በትንኝ አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከል ይኖርበታል::

ዝንቦች የትራኮማ በሽታንና ሌሎችም በርካታ የአንጀት ተውሳኮችን በማስተላለፍ ከፍተኛ የጤና ቀውስ የሚያደርሱ ነፍሳት ናቸው:: የእያንዳንዱ ግለሰብ ግቢ ወይም የማኅበረሰቡ አካባቢ ንጽህና በሚገባ ካልተጠበቀ በስተቀር ዝንቦች በቀላሉ እንዲራቡ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል:: ዝንቦች አዘውትረው በቆሻሻ ላይ የማረፍ፣ የመራባት እና የመመገብ የተፈጥሮ ባህሪ አላቸው:: ስለዚህ ከቆሻሻ አካባቢ ተነስተው ወደ ሰዎች መኖሪያ ቤት በመግባትና ከሰዎች ጋር በመኖር የሰውን ጤና የሚያውኩ በራሪ ነፍሳት ናቸው:: በአብዛኛው ዝንቦች የሚራቡት በሰው አይነ ምድር፣ በከብት እበትና ፋንድያ፣ በበሰበሰ ቆሻሻ (አዛባ)፣ በጥንቃቄ ባልተያዘ ስጋ፣ በምግብ ትርፍራፊና በሞቱ እንስሳት ላይ ነው::

የቤት ዝንብ አራት የእድገት ደረጃዎች አሏት:: እነርሱም እንቁላል፣ እጭ፣ ኩብኩባና በራሪ (ያደገች) ዝንብ በመባል ይታወቃሉ:: የዝንብ እድገት እንደ አየር ጠባዩ የሚለዋወጥ ቢሆንም የዝንብ እንቁላል ወደ ሙሉ በራሪ ዝንብ ለመለወጥ ከ6-42 ቀናት ይፈጃል:: ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ የዝንብ የሕይወት ኡደት ከ2-3 ሳምንት ብቻ


እንደሚፈጅ ይገመታል:: በቅዝቃዜ ወቅት እስከ 3 ወር ይፈጃል ተብሎ ይታመናል:: ዝንቦች ብዙውን ጊዜ ዕንቁላላቸውን የሚጥሉት በእንስሳት እበት/ፋንዲያ፣ ከቤት በሚወገድ ማንኛውም ቆሻሻ ላይ ነው:: የዝንብ እንቁላል ከ8-16 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ እጭ ይለወጣል:: እጩ ከ3-7 ቀናት ውስጥ ወደ ኩብኩባ ይለወጣል:: በአጠቃላይ ከ2-10 ቀናት ውስጥ እጩ ወደ በራሪ ዝንብ ያድጋል::

ዝንቦች በቆሻሻ ላይ ሲያርፉ የጤና ጠንቅ የሆኑ ተሕዋሲያንን በእግራቸውና በክንፋቸው እንዲሁም በሌላው የአካል ክፍል ተሸክመው በምግብ ዕቃዎች፣ በምግብና በሰው ላይ በማረፍ የያዙትን ቆሻሻ የማራገፍ ወይም የመቀባት እድል አላቸው:: ዝንቦች የበሉትን የማስታወክ ባህሪ ስላላቸው በአረፉበት ስፍራ ላይ ሁሉ ቆሻሻ ይተፋሉ:: በዝንብ የተበከለው ምግብ ሰዎች ሲበሉት የደም ተቅማጥ የወስፋትና ሌሎች የአንጀት ጥገኛ ትሎች፣ የአንጀት መታወክና ለሌሎቹም በሽታዎች ሊጋለጡ ይችላሉ:: ዝንቦች በተለይም የትራኮማ በሽታ ካለባቸው ሕፃናት ላይ አዘውትረው በማረፍ በሽታውን በስፋት ያሰራጫሉ::

**በዝንብ አማካይነት የሚከሰተውን የጤና ጠንቅ ለመከላከል ወይም ለማጥፋት ሊወሰዱ የሚገባቸው የመከላከያ እርምጃዎች:-**

- የመኖሪያ ቤትንና አካባቢን በንጽህና መጠበቅ፣
- የቤት ጥራጊ ቆሻሻን የምግብ ትራፊን ተስማሚ በሆነ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ አቆይቶ ቆሻሻ ጉድጓድ ውስጥ መጣልና ማቃጠል፣
- ማንኛውንም እጣቢና ሌላም ፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ጉድጓድ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በየስፍራው መዝረክረክ የለበትም፣
- የቤት እንስሳትን ከመኖሪያ ቤት ለይቶ በጋጥ ወይም በበረት ውስጥ ማሳደር፣
- እበትንም ሆነ ፋንዲያን በየቦታው እየሰበሰቡ በየጊዜው ጉድጓድ ውስጥ መቅበርና ከተብላላ በኋላ አውጥቶ ለጓሮ አትክልት ማዳበሪያነት መጠቀም፣
- ከእንስሳት እበት የኩበት ማገዶ ማዘጋጀት ሲያስፈልግ ከመኖሪያ ቤት ራቅ አድርጎ ማዘጋጀትና ማከማቸት፣
- የምግብና የመጠጥ ዕቃዎችን ማጠብና ምግብና መጠጥን በጥንቃቄ ከድኖ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፣
- ከተቻለ ምግብና የምግብ እቃ እንዳይበከል ጥንቃቄ በማድረግ የዝንብ መግደያ መድኃኒቶችን መጠቀም ሌላው አማራጭ ነው::

## 4.4 የመጸዳጃ ቤት አስፈላጊነት፣ አሰራርና አያያዝ



ሃገራችንን የተላላፊ በሽታዎች ምንጭ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የግልና የአካባቢ ንጽህና ጉድለት ነው:: በተለይም በገጠሩ ማኅበረሰብ የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም ያልተለመደ ስለሆነ አብዛኛው ቤተሰብ ዓይነ ምድርን በተገኘው ቦታ መጸዳዳት የተለመደ ነው:: ይህም ሁኔታ ለተላላፊ በሽታዎች መዛመት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል:: ዓይነምድርን የትምቦታ ከመጸዳዳት ይልቅ እያንዳንዱ ግለሰብ ቤተሰብና ድርጅት መጸዳጃ ቤት ሰርቶ በአግባቡ እንዲጠቀም ቢደረግ የትራኮማ በሽታን ጨምሮ እጅግ በርካታ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ይቻላል::

ሽንትና ዓይነ ምድርን በአደባባይ በየመንገዱ መጸዳዳት አካባቢን የሚበክል ከመሆኑም በላይ የእያንዳንዱን ግለሰብ ገመና የሚያጋልጥ ስለሆነ የሚደገፍ ተግባር አይደለም:: በዚህ ረገድ በተለይም በገጠሩ ማኅበረሰብ በየሜዳው መጸዳዳት ጸያፍና የጤና ጠንቅ የሚያስከትል ስለሆነ ይህ ድርጊት እንዲወገድ አስፈላጊው መሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መሰጠት አለበት:: ከዚህ በተረፈ ዓይነ ምድርን በየሜዳው መጸዳዳት:-

- በዓይነ ምድር አማካይነት ልዩ ልዩ በሽታዎች በየአካባቢው እንዲሰራጩ ያደርጋል፣
- በመኖሪያ ቤት አካባቢና በየሜዳው በሚገኘው ዓይነ ምድር ላይ ዝንቦችና ሌሎች ነፍሳት እንዲራቡ ያደርጋል፣
- ዝንቦችና ሌሎች ነፍሳት በዓይነ ምድር ከተበከሉ በኋላ በጸጉርና በእግራቸው አማካኝነት ባልተከደነ ምግብ፣ መጠጥ ወይም በምግብ ማቅረቢያ እቃዎች በተለይም በልጆች ዓይንና እንዲሁም በሌላ የሠውነት ክፍል ላይ በማረፍ ልዩ ልዩ በሽታዎችን በቀላሉ ያስተላልፋሉ፣
- በተለይም በክረምት ወራት በሚጥለው ዝናብ ምክንያት በሚከሰተው ጎርፍ አማካይነት ዓይነ ምድርንና የእንስሳት እበትና ፋንድያ በማሠራጨት የውሃ ምንጮችን እና የመኖሪያ አካባቢዎችን ስለሚበክል በአካባቢው ተስማሚ የሆነ የመጸዳጃ ቤት ሰርቶ ንጽህናውን በመጠበቅ መጠቀም ወሳኝነት አለው፣

## 4.5 ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ

መኖሪያ ቤት የሰዎችን አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ስነልቦናዊ ጤንነትንና ደህንነትን ለመጠበቅ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ መሠረታዊ ፍላጐቶች አንዱ ነው። በመሆኑም ሰዎች አብዛኛውን የህይወት ዘመናቸውን የሚያሳልፉት በቤት ውስጥ ስለሆነ ንጽህናው የተጓደለ መኖሪያ ቤት የትራኮማ በሽታን ጨምሮ በርካታ የጤና ቀውሶችን ሊያስከትል ይችላል።

ለጤና ተስማሚ ያልሆነ መኖሪያ ቤት ሰዎችን ለቅዝቃዜ፣ ላልተፈለገ ሙቀት፣ ለሚያበሳጭ ጭስ፣ ለሳንባ ነቀርሳ፣ ለእንፍሉዌንዛ ለግርሻና ተስቦ እንዲሁም ለትራኮማና ለሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጣል። ስነልቦናዊና ማኅበራዊ ቀውስን ያስከትላል። ለዚህ ዓይነቱ ችግር የሚጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአብዛኛው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ድሃ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲሆኑ ለዚህ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቂዎች የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑ ህፃናት፣ ሴቶችና አረጋዊያን ናቸው።

ስለዚህ ለጤና ተስማሚ የሆነ የመኖሪያ ቤት የሚባለው:-

- አላስፈላጊ ከሆነ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ በራሪ ነፍሳትና ተባዮች፣ ከፍተኛ ድምጽና አቧራ እንዲሁም ጭስ ከመሳሰሉት ለመከላከል የሚያስችል።
- በቂና ለጤና ተስማሚ የሆነ የውሃ አቅርቦት ያለው፣
- የመጸዳጃ አገልግሎት፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ የተሟላለት።
- ከተለያዩ አደጋዎች ለመከላከል የሚያስችል፣
- እንደ ቤተሰቡ ብዛት በቂ ክፍሎች ያሉትና በቂ የአየር ዝውውርና የፀሐይ ብርሃን ማስገባት የሚችል፣
- በማገዶ ጭስ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉትን የቤት ውስጥ የአየር ብክለት፣ የዓይን ጤና ችግር ለመከላከል የሚያስችል፣
- በቂ የአየር መውጫና መግቢያ በርና መስኮት ያለው፣
- ምግብ ለዝንብና ለሌሎች በራሪ ነፍሳት በመጋለጥ እንዳይበላሽ በቂ የሆነ ንጽህናው የተሟላ ማስቀመጫ መደርደሪያ ያለው።
- በሽታ አስተላላፊ ለሆኑ እንደ ዝንብ ለመሳሰሉ በራሪ ነፍሳት ተባዮችና ሌሎች ቆርጣሚ እንስሳት መራቢያነት አመቺ ያልሆነ፣
- በአካባቢው ውሃ፣ መዝናኛ ቦታና ለማኅበራዊ አገልግሎቶች ቅርበት ያለው እና የመሳሰሉት ናቸው።

ጤናማ የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች:-

- በተራራ ጫፍና ስር ያልሆነ፣
- አካባቢው ረግረጋማነት የሌለው፣
- ጐርፍ የማያጠቃው፣
- ለተፈጥሮ አደጋዎች (የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ናዳ፣ የመሬት መንሸራተት) ያልተጋለጠ፣
- በደልዳላና መጠነኛ ተዳፋት ባለው ስፍራ ላይ የተሰራ፣
- አፈሩ በቀላሉ ውሃን ሊመጥ የሚችል፣
- ንጹህና በቂ ውሃ የሚገኝበት፣
- ውሃን አፈርንና አየርን ከሚበክሉ ሁኔታዎች የራቀ፣
- የፀሃይ ብርሃንና በቂ አየር በቀላሉ ማግኘት የሚችል፣
- ከቆሻሻ መጣያና ከፍተኛ ድምጽ ከሚፈጠርባቸው ቦታዎችና ከመሳሰሉት የራቀ መሆን ይገባዋል::

## 4.6 የመኖሪያ ቤት ንጽህና አጠባበቅ

- ቤትን በየጊዜው መጥረግ፣ ወለሉን ማጽዳት፣ ምንጣፍ ካለ (ሰሌን ጀንዲ እና የመሳሰሉት) በሣምንት አንድ ጊዜ እያወጡ ማራገፍና ማናፈስ፣
- የቤት ግድግዳና ወለል ለበራሪ ነፍሳትና አይጦች መደበቂያ እንዳይሆን ማድረግ፣
- በቤት ውስጥም ሆነ በአካባቢው ማንኛውንም አይነት ቆሻሻና ትርፍራፊ ምግብ እንዳይከማች ማድረግና በአግባቡ ማስወገድ፣
- ማንኛውንም የቤት ውስጥ እጣቢና ፍሳሽ ቆሻሻን በቦይ እንዲወገድ ማድረግ፣
- ደረቅ ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠል ወይም በመቅበር ማስወገድና የመሳሰሉት ናቸው::

ማንኛውም ጤናማ የመኖሪያ ቤት የሚከተሉት መገልገያዎች ሊሟሉለት ይገባል:-

**4.6.1 ማዕድቤት (ምግብ ማዘጋጃ):-** ከመኖሪያ ቤት የተለየ ክፍል ሆኖ ከመጸዳጃ ቤት፣ ከጠጣር ቆሻሻ ማከማቻ እንዲሁም ከእንስሳት ማደሪያ የራቀ መሆን አለበት:: የዚህም ዋናው ጥቅም ምግብ በሚዘጋጅበት ጊዜ በቤት ውስጥ በጢስ የመታፈን ችግር እንዳይከሰትና በሰው ጤንነት ላይ ከፍተኛ ችግር

እንዳይከሰት ለማድረግ ነው:: ለምሳሌ የዓይን ህመም፣ የመተንፈሻ አካል ችግር፣ ለእሳት አደጋ መጋለጥና የቆዳ በሽታ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ::

**4.6.2 የመጸዳጃ ቤት:-** ማንኛውም ጤናማ የመኖሪያ ቤት የመጸዳጃ ቤት ሊዘጋጅለት ይገባል:: ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣ ሽታ በጤንነት ላይ ችግር እንዳይፈጥር መቀመጫው ክዳን እንዲኖረው ማድረግና የነፋስ አቅጣጫን ተከትሎ አየር እንደልብ የሚዘዋወርበት ሊሆን ይገባዋል:: የመጸዳጃ ቤትን ንጽህና ለመጠበቅ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ቆሻሻው ሞልቶ ሳይዝረከረክ በአካባቢው መጥፎ ሽታና የዝንብ መራቢያ እንዳይሆን ከስር ከስር በአግባቡ ማስወገድ ይገባል:: ምንጊዜም ቢሆን ማንኛውም መጸዳጃ ቤት የዝንቦች መራቢያ እንዳይሆን ክዳን እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል::

### 4.6.3 የቤት እንስሳት ማደሪያ ቤት (ጋጥ/በረት)

በሀገራችን በገጠሩ አካባቢ እንስሳትና ሰው በአንድ ቤት ውስጥ ማደር የተለመደ ነው:: በዚህ ምክንያት ቤቱ በንጽህና ጉድለት ሳቢያ የዝንብ መራቢያ ስለሚሆን የቤተሰቡ አባላት ለትራኮማና ለሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ይጋለጣሉ:: በመሆኑም የመኖሪያ ቤት ለጤና ተስማሚ እንዲሆን ወይም አካባቢው እንዳይበከል የእንስሳት ማደሪያ ቤት ከሰዎች መኖሪያ ተለይቶ ከውሃ መገኛ ምንጭና ከምግብ ማዘጋጃ ሥፍራ ራቅ ብሎ መሠራት አለበት:: የእንስሳትን ጤንነት ለመጠበቅና የእንስሳት ማደሪያ ቤት በየእለቱ መጠረግና መናፈስ ይኖርበታል:: በቂ የአየር ማስገቢያ ሊኖረው ይገባል:: ወለሉም ደልዳላና በቀላሉ ሊጠረግ የሚችል ሊሆን ይገባዋል:: በቂ የተፈጥሮ ብርሃንና አየር ማስገቢያ፣ መስኮትና በር፣ የእንስሳት ማሰሪያ፣ መመገቢያና ወሃ መጠጫ ገንዳ ያለው መሆን አለበት::

## ማጠቃለያ

ጤና በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ ያለመሆን ብቻ ሳይሆን የተሟላ የአካል፣ የአእምሮና የማኅበራዊ ኑሮ ደህንነት ማለት ነው። ዛሬ በዓለም ላይ ያለው የጤና አገልግሎት ሲታይ እጅግ በጣም የተዛባ ነው። በኢኮኖሚ የበለፀጉና በሥልጣኔ የመጠቁ አገሮች ተላላፊ በሽታዎችንና ሌሎችንም የጤና ጠንቆች በቁጥጥር ስር በማዋል የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ በይበልጥ በማሻሻል ላይ ይገኛሉ። የታዳጊ ሀገሮች ሕዝቦች ግን ለበርካታ ተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ በመሆናቸው የጤንነታቸው ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ትራኮማ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ጋር የተቆራኘ፣ በተለይም በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት በሌለበት፣ የተመቻቸ የጤና አገልግሎት እንደ ልብ በማይገኝበት፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና ባልተሟላበት፣ የሕዝብ ብዛትና ተፋፍጎ የመኖር ችግር በሚታይበት ሥፍራ ሁሉ በስፋት ተሰራጭቶ የሚገኝ ተላላፊ በሽታ ነው።

ሴቶች በማርገዝ፣ በመውለድና በማጥባት፣ በቤትና በመስክ ስራ በመሰማራትና በአጠቃላይ ቤተሰብን በመንከባከብ በሚደርስባቸው የተዛባ የሥራ ጫና ምክንያት አቅማቸው የተዳከመ በመሆኑ ለማንኛውም በሽታ በቀላሉ ሊጠቁ ይችላሉ። ከሁሉም በላይ ጊዜውና አቅሙ ስለሌላቸው የራሳቸውንም ሆነ የልጆችን የግል ንጽህና ለመጠበቅ ስለማይቻላቸው በትራኮማ በሽታ ምክንያት ለሚከሰተው የዓይነ ስውርነት በመጠቃት ለልመናና ለጎዳና ተዳዳሪነት እየተጋለጡ ናቸው።

ይህ ዓይነቱን የጤናና የማኅበራዊ ችግር ለመፍታት ከሁሉ አስቀድሞ መሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት ተገቢ ነው። ?መልካም አስተዳደር መኖርም ያስፈልጋል። የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ማግኘት ደግሞ ሌላው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ህብረተሰቡ እነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች እስከተመቻቹለት ድረስ አወንታዊውን ነባር ልምዱን፣ ጉልበቱንና በሥልጠና ያገኘውን ክህሎት በማቀናጀት ችግሩን ለመቅረፍ በግንባር ቀደም ሊሰለፍ እንደሚችል አይጠረጠርም። በዚህ ረገድ ውጤታማ የሆነ ሥራ ለማከናወን የተቀናጀ እና መንደር አቀፍ የትራኮማ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ብሎም ዓይነ ስውርነትን ለማስወገድ የሚያስችል የተቀናጀ መርህ ግብር ነድፎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ይህን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በአጠቃላይ የህብረተሰቡ በተለይም የሴቶች ግንባር ቀደም ሚና መጫወት አስፈላጊ ቢሆንም ተገቢውን የዕውቀት፣ የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ለማግኘት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ በሥራ መስኩ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ እንዲሁም ሌሎች ለጋሽ በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር የፈንጣጣ፣ የጊኒ ወርምና የፖሊዮ በሽታዎችን በማጥፋት የተገኘውን ድል በትራኮማ በሽታና በዓይነ ስውርነት ላይ መድገም እንደሚቻል ብሩህ ተስፋ ይታያል።

## ዋቢ መረጃ


1. TRACHOMA: A Women's Health Issue Revised Edition, Elaine M. Wolfson, Ph.D., Lori Fedewa, and Stacie A. Young, The Global Alliance for Women's Health.
2. Achieving Community Support for Trachoma Control, A guide for district health work, Victoria Francis and Virginia Turner
3. Woltson, E.M, Fedewa, and Young S.R, 1997, 1999, The Alliance For Women's Trachoma: A Women's Health Issue, Pages 2, 6, 8
4. Nemageher, W. Etal (2004) Surgery for Trichiasis by Ophthalmolmologists versus Integrated Eye care workers, Randomized.
5. UN Population Fund 2000, Key Actions for Further Implementation of the program of Action of International conference on population and Development, New York, P. 16 Paragraph 46.
6. UNICEF (  ) First call for children; Convention on the rights of children, new York Paragraph 11.
7. በጤና አጠባበቅ ኤክስቴሽን መርሃ ግብር *የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ፓኬጅ*፣ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሐምሌ 1994::
8. በጤና አጠባበቅ ኤክስቴሽን መርሃ ግብር *ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሠራርና አጠባበቅ ፓኬጅ* ፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሐምሌ 1994::
9. በጤና አጠባበቅ ኤክስቴሽን መርሃ ግብር፣ *የተባዮችና ቆርጣሚ እንስሳት መከላከልና ቁጥጥር ፓኬጅ* የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሐምሌ 1994
10. በጤና አጠባበቅ ኤክስቴሽን መርሃ ግብር *የውሃ ንጽህና አጠባበቅ ፓኬጅ* የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሐምሌ 1994